# Edutainment

## አጫጭር ገጠመኞች

## ተለያየን

‹ተለያየን› ሲባል ሰምተው ያውቃሉ? በተለያዩ አገባቦች ተለያየን ሲባል ይደመጣል፡፡ ብዙ መነሻዎች ሊኖሩት ይችላሉ፡፡ አንዱን አሁን እዚሁ እነሆ፡- ወሎ ውስጥ ኩታ በር በሚባል ከደሴ በስተ ምዕራብ በኩል ወጣ ብሎ በሚገኝ ቦታ አንድ ወንዝ አለ፡፡ ስሙ ‹ተለያየን› ይባላል፡፡ የስሙን አወጣጥ ለማወቅ በአዲስ አንቀጽ እንገናኝ፡፡

አንዲት እናትና ሴት ልጃቸው ለጉዳያቸው ከቤት ወጥተው ውለው አመሻሽ ግድም ከዋሉበት ይመለሳሉ፡፡ ቀድሞ በሌላ ስም ይጠራ በነበረው ወንዝ ዳርም ሲደርሱ ልጅ መቼም ቀዥቀዥ ማለት ይወዳልና እናትዮዋ ለተፈጥሮ ጥሪ ወይም ለሌላ ጉዳይ ወደ ኋላቸው ቀረት ሲሉ ልጂት ትቸኩልና ወንዙን ማቋረጥ ትጀምራለች፡፡ ነገር ግን በደጋው አካባቢ ዝናብ ጥሎ ኖሮ ፈረሰኛ ጎርፍ እየጋለበ ድንገት ይመጣና ጉልበቷ ያልጠና ልጂትን አፈፍ አድርጎ ከግንዱና ከድንጋዩ በማደባለቅ እያገለባበጠ ቁልቁል ይዟት ይተምማል፡፡ ይሄኔ የልጃቸውን በጎርፍ ውኃ መበላት የተረዱት እናት በድንጋጤ ክው ብለውና ዕንባም ከድቷቸው ‹ልጄ፣ ተለያየን? ልጄ፣ ተለያየን?› አሉ ይባላል፡፡ በዚያም ምክንያትና ከዚያ ወዲህ የወንዙ የቀድሞ ስም ተለውጦ ‹ተለያየን› ተብሎ እንደሚጠራ ይነገራል፡፡ በዚህ መልክ ብዙ ስያሜዎች መነሻ እንዳላቸው ልብ ይሏል፡፡

ሰዎች በሀብት፣ በዕውቀት፣ በትምህርት ደረጃ፣ በዕድሜ፣ በፆታ፣ በሃይማኖትና በመሳሰሉ ጉዳዮች እንደሚለያዩ ይታወቃል፡፡ ልዩነቶች ሁሉ ደግሞ የራሳቸው ጠቃሚም ሆነ ጎጂ ጎን አላቸው፡፡ እንዲያውም የአንዳንድ ልዩነቶች መኖር የግድ ያህል እንጂ የምርጫ ብቻም አይደለም፡፡ ለምሣሌ የፆታ ልዩነት ባይኖር በምድር ላይ አንድም ሕይወት ሊኖር ባልቻለ ነበር፡፡ እርግጥ ነው አሜባን የመሳሰሉ ኢወሲባውያን ፍጡራን ብቻቸውን ሊርመሰመሱ ይችላሉ፡፡ የአንዳንድ ልዩነቶች መኖር ደግሞ የግድ ያህል ባይሆንም በተፈጥሯዊነቱ ተቀብለን ብዙም ሳይከፋን ተቻችለን እንኖራለን - ሰዎች፡፡ ለምሣሌ አንዱ ዶክተር ይሆናል ሌላው ምንም ሳይማር የቀን ሠራተኛ ሊሆን ይችላል፤ አንዱ ሙስሊም ይሆናል ሌላው ክርስቲያን ወይም እንዲሁ ያላንዳች ሃይማኖት ቢስሚላሂም በስማምም ሳይል በኢአማኒነት ራሱን ወስኖ ሊኖር ይችላል፤ የብዙ ነገሮች የመሆንና ያለመሆን ምርጫ የራሳችን ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተጠቆመው ልዩነቶች ሁሉ ሲጤኑ አንዳንዶች መልካም ጎን አላቸው፤ አንዳንዶች ደግሞ ጎጂ ጎን ሊኖራቸው እንደሚችል መረዳት አይከብድም፡፡ የልዩነቶች ጎጂ ጎን ግዘፍ ነስቶ ጎልቶ ሊታይ የሚችለው ግን በአያያዝ ጉድለት እንደሆነ መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡ እኔ ከእርስዎ በማንኛውም ረገድ አንድ እንድሆን አይጠበቅብኝም፤ ልሆንም አይቻለኝም፡፡ በመጀመሪያ ሁሉም አንድ ቢሆን ሕይዎት ጣዕም የላትም፤ አሰልቺ ትሆናለች፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ሁላችንም አንድ ዓይነት ሥነ ሕይወታዊ ቀመርና አካባቢያዊ ገጽታ የለንም፡፡ ዋናው ግን የልዩነት መሠረቶችን በማክበር በልዩነቶች ሰበብ አንዱ አንዱን አለመናቅ ወይም በተቃራኒው ጓሊናን ስቶ አለማጎብደድ የሚገባ መሆኑን መረዳት ነው፡፡ በቃ፡፡ ያኔ ልዩነቶች የቅራኔ መንስኤ ከመሆን ይታቀቡና የመግባባትና የመቻቻል ዐውዶች ይሆናሉ፡፡

መግቢያየ በዝቶ ተንዘላዘለብኝ እንጂ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ በኔም ላይ ሆነ በወዳጆቼ የደረሰባቸውን አስገራሚ ገጠመኞች ለመጠቆም ነበረ፡፡ ይቅርታችሁ እስካልተለየኝ ድረስ ብዙ የዘገየሁ አይመስለኝም፡፡

አንድ ወዳጄ እንዲህ አለኝ፡፡ ከጓደኛው ጋር በአካልም በመንፈስም ከተለያዩ ብዙ ጊዜያቸው ነው፡፡ ከበርካታ ዓመታት በኋላ ሲገናኙ ታዲያ የደንቡን ባህላዊ ሰላምታ በፍቅርና በናፍቆት ይለዋወጡና በሕይወታቸው ዙሪያ አንዳንድ ጉዳዮችን እያነሱ ይጫወታሉ፡፡ በመጀመሪያ የሁለቱም የንግግር ድምፀት እኩልና ጓደኛዊ/የወዳጅነት ነበር፡፡ ቀስ እያለ ግን የዚያኛው ጫፍ ድምፀት(ቶን) መለወጥ ይጀምራል፡፡ ያም የሆነው የኔው ጓደኛ እስከዚያን ወቅት ድረስ በማስተርስ ዲግሪ ብቻ ተወስኖ መቆየቱን ለባለ ፒ ኤች ዲው ጓደኛው በመግለጹ ምክንያት ነበር፡፡ ይህ ልዩነት በመሠረቱ ከፍ ሲል እንደጠቆምኩት ጤናማና የማንንም ሕይወት በአሉታዊ ጎኑ የማይነካ ነው፡፡ ማንምም ቢሆን ፈቃደኝነቱና ፍላጎቱ ካለው፣ ዕድሉንም ካገኘ የትኛውም የትምህርት ደረጃ ላይ ለመድረስ የሚገድበው ነገር የለም፡፡ ባጋጣሚም ይሁን በይሁንታ ማንም ሰው በትምህርት መሰላል ወደላይ ወጥቶ የዶክትሬት ዲግሪ አለመያዙ የዓለም ፍጻሜን አይጋብዝም፡፡ በዲግሪ መለያየት ይህን ያህል የሚያሸካኩበት አይመስለኝም፤ አይደለምም፡፡ እንዲያውም ሰው በተማረና በተመራመረ መጠን ይበልጥ ትሁትና አስተዋይ ሊሆን ይጠበቅታል እንጂ እስከዚህ ወርዶ ደደብና ንክር ሊሆን አይገባም ብዬ አምናለሁ፤ ለትክክለኝነቴም ዋቢ መጥቀስ ሳያስፈልገኝ በተገቢው መንገድ ሰው የሆነ ሰው ሁሉ የሚረዳው ነባራዊ እውነት ነው፡፡ ያ ‹ጓደኛ›ው ለጓደኛየ ይባስ ብሎ ‹ተለያየና› ብሎ የተማረ ማይምነቱን

እንደገለጠለት አጫውቶኛል፡፡ ሰው መቼም ከነንፍጡ ካልወደድነው በስተቀር ስንትና ስንት ገመና አለብን መሳላችሁ?

እኔም እንዲህ ሆኛለሁ፡፡ አንድ ወቅት የልጅነት ጓደኛየን ፒያሣ አካባቢ አገኘዋለሁ - ከሃያ አምስት ዓመታት ገደማ በፊት ነው፡፡ ሰላምታ እንለዋወጥና ስለትምህርት መጠያየቅ እንጀምራለን፡፡ ‹እንዴት ነው ትምህርት?› ብዬ ስጠይቀው በአንድ የመንግሥት ዩኒቨርስቲ በዲግሪ እንደጨረሰ፣ በጥሩ መሥሪያ ቤትም እንደተመደበ በልዩ መጀነን ይነግረኛል፡፡ ልጁን በልጅነታችን ሳውቀው ጉረኛ ቢጤ ስለነበር እንዲያ መሆኑና ምድርን መጠየፉ ብዙም አላስገረመኝም፡፡ የተፈጥሮ ነገር ሆኖ ብዙዎቻችን ብዙ ድራቢ ባሕርያት አሉብን - መቻቻል ነው፡፡ ለዚሁ ጓደኛየ የኔንም አንሻፍፌ ነገርኩት - ጉዱን ለማየት፡፡ ‹የኔን ነገር አታንሳው፤ እንዲያው ተከድኖ ይብሰል ባክህ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለሁለት ዓመት ከተማርኩ በኋላ ትንሽ አመም ያደርገኝ ስለነበርና በደንብ ማጥናት ስላልቻልኩ ተባረርኩ፡፡ …› አልኩት፡፡ ያኔ ማርሽ ለወጠ፤ ሽቅብ ተወነጨፈ ማለት ይቀላል እንደ አፖሎ የናሳ መንኮራኩር፡፡ ‹እናስ፣ እንዴት ትኖራለህ?› አለና ጠየቀኝ ሌባ ጣቱን አፍንጫው ላይ ሰግጦ፡፡ ‹እንደምንም፡፡ ፈጣሪ ጥሎ አይጥልም መቼም እህቴ ጥቂት ሣንቲም ትወረውርልኛለች - በዚያች እኖራለሁ፡፡› አልኩት፡፡ አካላዊና ሥነ ልሣናዊ ለውጦቹን እየተከታተልኩ መሆኔን እንዳትረሱ፡፡ ሰውነቱን እንደእፉኝት መነፋፋቱንና በቅላፄው መንቀባረሩን በጉልህ መረዳት በሚቻልበት ሁኔታ ቀጥሏል፡፡ አያድርስ ነው፤ እንዲህ ዓይነት ወላዋይ አቋም ያለው ሰው በርግጥ ያናድዳል፡፡ ቀስ አልኩና የጨዋታውን ሜዳ እኩል የምንጠቀምበትን ሁኔታ ወደማመቻቸቱ ገባሁ - አለበለዚያ እንደተሰቀለ ልንለያይና ስለ እኔ እውነት ያልሆነ ነገር ሊበትን ነው፡፡ ቀጠልኩ - ‹ ያልኩህን ነገር ስቀልድ ነው እንጂ እንዳንተው ጨርሻለሁ፡፡ የተመደብኩበት መሥሪያ ቤትም …› አልኩና በወቅቱ የገደል ስባሪ ከሚያካክሉ አስፈሪ መሥሪያ ቤቶች የአንዱን ስም ጠርቼ እዚያ እንደምሠራ ውስጡን በውስጥ ዐይኖቼ እየሰለልኩ ነገርኩት፡፡ ያ ልጅ እንደወጣ እዚያው ተንጠልጥሎ እንዲቀር አልወደድኩምና ትዝብትና ይሉኝታ ሳይበግሩት ተኮፍሶ ተቀምጦበት ከነበረው የኩራት ማማ በወጣበት መሰላል በአንዴ ተንኮታኩቶ ሲወርድ በግልጽ ታየኝ - ለምቀኝነት አይደለም ይህን ያደረግሁት፤ ቢገባው እንዲማርበት እንጂ፡፡ ከአፍታ ቆይታ በኋላ እኔም እንደሌላ ጊዜው ሁሉ የሰዎችን በአላስፈላጊ ሁኔታ የመለዋወጥ እስስታዊ ባሕርይ ተረድቼ ተለያየን፡፡ ይህን ዓይነት የስሜትና የቋንቋ ቃና መዘበራረቅ የሚያስከትለው የራስ የሚሉት ቋሚና ወጥ የሆነ አቋም ያለመያዝ ውጤት ነው፡፡ ራስን መሆን አለመሆን በሚሉት ልማዳዊ አባባል ብዙም አላምንም፡፡ ለምን ቢባል ሰው ሁሉ ራሱን ሳይሆን አይኖርምና፡፡ ውሸታም ሰው አዘውትሮ ከዋሸ ራሱን ሆንዋል - ውሸታም፡፡ ጉረኛም ሰው አዘውትሮና እንደልማድ አድርጎ ጉረኝነቱን ከያዘ ራሱን ሆንዋል - ጉረኛ፡፡ የሚያጭበረብርም ሰው በማጭበርበር ‹ሙያ›ው ራሱን ሆኖ በዚያው ይታወቃልና ራሱን ሆንዋል - አጭበርባሪ፡፡ የሚሴስንም ሰው በዚያው የራስ መግለጫ የማንነት ምግባሩ ይታወቃልና ራስን ያለመሆን ችግር ስለሌለበት ራሱን ሆንዋል - ሴሰኛ፡፡ በዚህ የጉዞ መስመር ብዙ መግፋት ይቻላል - የራስ ማንነትን መግለጫ መንገዶችን በመግለጽ ረገድ፡፡ ስለዚህ ሰው ራሱን መሆን የሚችልባቸው በርካታ አሉታዊና አወንታዊ ጎኖች አሉ ብዬ ስለማስብ ይሄ ‹ራስህን ሁን› የሚሉት ፈሊጥ እንደነገርኳችሁ ብዙም አይገባኝም፡፡ ብቻ ተፈጥሮአዊና መናኛ ልዩነቶችን ይዞ ‹ተለያየን› እያለ ከሚያሳቅቅ ጓደኛ ይሠውረን፡፡

## አንድ ቀፀላ!

በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር በሰባዎቹ መጀመሪያ አካባቢ ነው፡፡ አንድ አካባቢ አገልግሎት ይሰጥ በነበረ አንድ ሆቴል ውስጥ የተከሰተ ነገር ነው፡፡ ‹ቀፀላ› እሚባል በአካባቢው እሚታወቅ ሰው ሆቴሉ ውስጥ እየገባ አስተናጋጆችን ይጠራና ለማ'ድ ቤት ሠራተኛዋ ‹አንድ ቀፀላ› ብሎ እንዲነግራትና ይዞለት እንዲመጣ ያዛል፡፡ አስተናጋጁም ማ'ድ ይሄድና በልማዳቸው መሠረት ጮክ ብሎ ‹አንድ ቀፀላ› በማለት ይናገራል፡፡ ምግቡ ፍርፍርም ይሁን ጥብስ ሽፍንፍን ብሎ በልዩ ሁኔታ ይሠራና ላዘዘው ሰው ይቀርባል፡፡ የሥጋው ይዘት፣ ቅቤው፣ ቅልጥሙ ለጉድ ነው፡፡ ሌላ ሰው ሲያዝ ግን አቀራረቡ መናኛና ዘወትራዊ ነው- ለማንም ተራ ደንበኛ እንደሚቀርበው፡፡ የዚህ ሰውዬ ምሥጢራዊ ዕንቆቅልሽ ሲደረስበት ምን ሆኖ ተገኘ መሰላችሁ - ከሠራተኛዋ ጋር ጋቢ ተጋፏል፡፡ የቀፀላ ስም ሲነሣ አንሶላ ተጋፋፊዋ የሥራ ትዕዛዙን በቀጥታ ትቀበልና እርሷው ናት ሠርታ የምትልክ፡፡ የዚህን ሰው ውስጠ ነገር የተረዱ ሌሎች ደንበኞችም ‹አንድ ቀፀላ› እያሉ በማዘዝ ሁኔታው የአደባባይ ምሥጢር ሆኖ ከመጋለጡና የማስተካከያ እርምጃ በሆቴሉ ማኔጅመነት ከመወሰዱ በፊት ለተወሰነ ጊዜ ከሳላይሰጥና ከጎድን አጥንትና ከባዶ የቀይ ሽንኩርትና የቲማቲም ፍርፍር ተላቀዋል ይባላል፡፡ ለጎኑ ያወቀ ብልህ **ቀፀላ** አይደለም?

## ብልጥ ለብልጥ

ዘመኑ ብልህነት የቀነሰበት ብልጥነት ግን የተንሠራፋበት ይመስላል፡፡ አንዱ ምግብ ቢጤ ቀርቦለታል፡፡ ጎረቤቱ አጠገቡ ተቀምጧል፡፡ ቢጠብቅ ቢጠብቅ ከቤት አልወጣና አልሄድለት ስላለ ነው የ‹እንብላ›ን ባህል ተወት በማድረግ ብቻውን ሊበላ እጁን ታጥቦ የተሠለፈው፡፡ እንደወጉ ምግብ ሲቀርብ በቤት ውስጥ ያለ ሁሉ እጁን ታጥቦ አብሮ እንዲበላ ነበር እሚደረግ፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን ያ በጭራሽ የማይሞከር ነው፡፡ ኑሮው ስለተወደደ ዘግቶ በልነት እንደንፉግነትና ገብጋባነት የሚያስቆጥር ሳይሆን ኑሮን በዘዴ ጦምን በኩዳዴ እንደማለት ያህል አዋጪ ዘዴ ሆንዋል፡፡ ይህ ዓይነቱ ሊለመድ የሚገባው አዲስ ባህልም ከነውርነት ከመቆጠር እየወጣ ለመኖር አስፈላጊ ከሆኑ የጊዜያችን የጎልውና ሥልቶች አንዱ ወደመሆን ደረጃ ደርሷል፡፡

ሊለመድ የሚገባው አዲስ ባህልም ከነውርነት ከመቆጠር እየወጣ ለመኖር አስፈላጊ ከሆኑ የጊዜያቸን የጎልውና ሥልቶች አንዱ ወደመሆን ደረጃ ደርሷል፡፡

በመግቢያችን የጠቀስነው ብልጥ ሰውዬ ጎረቤቱ አፍጥጦ ቢጠብቅና አልወጣ ቢል ጊዜ ምን አለ መሰላችሁ፤ ‹መቼም እንብላ ቢሉህም እሺ አትልም› አለና ጎረቤቱን በይሉኝታ ገመድ ጠፍንጎ ብቻውን ሊበላ እጁን ወደ ማዕዱ ከመስደዱ ብልጡ ጎረቤት ምን አለ መሰላችሁ - ‹እምቢ ቢሉህም ችግር ነው› ይልና አብሮ መብላቱን ቀጠላ! አያድርስ ነው እንጂ ምን ይባላል?

## ‹ጎበዙ ተማሪ›

ፈተና ባይኖር ሁሉም ተማሪ ያው ተማሪ ነው፡፡ የጥንት አባቶች፣ ‹የሴትነት መለያው የማጀቱ ሙያ ባይኖር ኖሮ ሁሉም ሴት እኩል ሴት ነው› እንደሚሉት ዓይነት መሆኑ ነው፡፡ ሃምሣ ተማሪ ያለበት የመማሪያ ክፍል ውስጥ በሴሚስተር መጨረሻ አንዱ አንደኛ ሲወጣ ሌላውና የዚያው ክፍል አባል የሆነው ተማሪ ሃምሣኛ ይወጣል፡፡ መበላለጥ የነበረ፣ ያለና የሚኖርም ነው፡፡ በዚህ ሂደት ታዲያ በርትቶ ማጥናትና አለማጥናት፣ የሚጠናን ከማይጠና ለይቶ ለፈተናዎች በደንብ መዘጋጀትና አለመዘጋጀት፣ ያጠኑትን ነገር በአእምሮ መዝግቦ መያዝና አለመያዝ የራሳቸው አወንታዊና አሉታዊ ጎን አላቸው፡፡ ጎበዝ ተማሪ የምንለው እንግዲህ ሁነኛ የአጠናን ሥልትን በመከተል ፈተናንና ትምህርታዊ የክፍልና የቤት ሥራዎችን በትጋትና በብቃት የሚያከናውን ማለት ነው፡፡

አንድ ተማሪ ነው - እዚሁ አዲስ አበባ ውስጥ፡፡ በአንድ ፈተና ላይ የቀረቡለትን የፈተና ጥያቄዎች አንዳቸውንም ሳያውቃቸው ይቀራል፡፡ የመልስ መስጫ ወረቀቱ ላይ ለተወሰኑ ደቂቃዎች አፍጥጦ ከቆዬ በኋላ ከአእምሮው የሚታለብና በመልስነት የሚያገለግል ነገር በፍፁም ሲያጣ ጊዜ የመልስ መስጫው ወረቀት ግርጌ ላይ ምን ብሎ ጻፈና ወጣ መሰላችሁ - ‹መልሱን ባውቀው ኖሮ ምን ቸገረኝ?›፡፡ ምን ለማለት ነው - ‹መልሱን ባውቀው ለምን እደብቃችኋለሁ? እጽፈው ነበር እንጂ› ማለቱ ነው፡፡ ሰው በብድርም ይሁን በስጦታ መልክ ገንዘብ ሲጠይቀንና ሳይኖረን ሲቀር ‹ ቢኖረኝ ኖሮ ምን ቸገረኝ፤ እሰጥህ አልነበረምን?› እንደምንለው ነው፡፡

## አንቺን ካሸካነነሽ …

በዱሮ ጊዜ ነው፡፡ ጎንደር ውስጥ በአንድ የሠርግ ድግስ ላይ ነው የተፈጸመው ይህ እውነተኛ ታሪክ፡፡ ከታዳሚዎች መካከል ሁለት ባልና ሚስት ከሌሎቹ ሠርገኞች ጋር በዳሱ ውስጥ ይጨፍራሉ፡፡ መጠጥ አለ፤ ሁካታ አለ፡፡ ያን ተከትሎም ሞቅታና ስካርም የሚጠበቁ ናቸው፡፡ የሰውነት መሞቅ ሲኖር ደግሞ የአእምሮ ጤንነት ይናጋል፤ ስሜታዊነት ይገንና ምክንያታዊነት ይደበቃል ወይም ቢያንስ ለጊዜው ከነአካቴውም ሊጠፉ ይችላል፡፡ ተጠቃሽ ባልና ሚስት ከታዳሚዎች ጋር መጨፈራቸውን ቀጥለዋል፡፡ ሚስት ሕጻን ልጅዋን አዝላ ከጎረምሣ ጋር ጭፈራውን ታቀልጠው ይዛለች፡፡ ባል ተረሳ፤ ትዳር ተዘነጋ፤ ቤት ንብረት ከጎሊና ጓዳ ተሠወረ፡፡ የታዘለ ልጅም ከመጤፍ ተቆጠረ፡፡ በጭፈራው ድምቀት ዓለም አለፈች፡፡ መጠንን ያለፈ ደስታ ደግሞ መጠንን ያለፈ ልቅሶ ማስከተሏ ብዙውን ጊዜ የሚጠበቅ ነውና አብሯት በሚጨፍረው ጎረምሣ የዓይን ፍቅር ልቧ የተነደፈው እመጫት በግጥም እንዲህ ትላለች፤

*እኔስ አሸካነነኝ፣ እኔስ አሸካነነኝ፤*
አንቀልባ *ግዛና ልጅህን ተቀበለኝ፡፡*

ባልም ለመልሱ ቅጽበታዊ ምላሽ ከመስጠት ቅንጣት አላፈገፈገም - የጠረጠረው ነገር ነፍስ ዘርቶ በገሃድ በመውጣቱና በሰው ፊት በመዋረዱ ክፉኛ በቁጭት ተንገብግቦ እንዲህ ሲል አጸፋውን በግጥምና በግብር ሰጠ፡-

*አንቺን ካሸካነነሽ እኔም አሸካነነኝ፤*
*ባማሪካን ጥይት በላት በላት አለኝ፡፡*

ግጥምን በግጥም ከመመለሱ ጎን ለጎን ትከሻው ላይ የነበረውን ሞይዜር ጠበንጃ በማውረድ በርከክ ብሎ በዚያች የጎረምሣ ፍቅር ምርኮኛ እመጫት ላይ ደጋግሞ ተኮሰባትና ወዲያውኑ ገደላት - ጥይት ከነመረቁ እሚባለው አገዳደል የዚህ ዓይነቱ ነው፤ መጥፎ አጋጣሚ፡፡ ሠርጉም ወዲያውኑ ወደ ሀዘን ተለወጠ፡፡ ሰይጣንም ጀብድ ሠራና ተሾመ፤ ተሸለመ፡፡ ከዚህ ዓይነቱ መቅሰፍት ይጠብቅ፡፡ ‹አፍ ይፀውዖ ለሞት›(አፍ ሞትን ትጠራለች) እሚባለው ይህን ዓይነቱን መጥፎ አጋጣሚ ለማመልከት ነው፡፡

## የስም አወጣጥ ነገር ሲነሣ

የስም አወጣጥ እንደየሀገሩና ባህሉ የተለያዬ ነው፡፡ በስያሜ ዙሪያ በርካታ የመመረቂያ ጽሑፎችም ተጽፈዋል፡፡ ኬነዲ ቤተ መጻሕፍትን ካጨናነቁ የመመረቂያ ጽሑፎች ውስጥ ቀላል ቁጥር የሌላቸው ወረቀቶች በዚህ በስያሜ ዙሪያ የተሠሩ መሆናቸውን መገመት አይገድም፡፡

ስያሜ ሲባል የቦታ አለ፤ የሰው አለ፤ የዕቃና የእንስሳትም ሁሉ አለ፡፡ በሀገራችን የተወሰኑ አካባቢዎችን የስም አወጣጥ ስናይ ብዙ የሚያስገርሙን ነገሮችን እናገኛለን፡፡ ሰዎች ለውሻቸው ስም ሲያወጡ ‹መቻል› ወይም ‹ችሎ ማደር› ሲሉ ማስተላለፍ የፈለጉት መልእክት መኖሩን እንረዳለን፡፡ ለልጃቸውና ለቦታዎች የሚሰጡት ስያሜም ብዙውን ጊዜ ከአንዳንድ ገጠመኞቻቸው ጋር እንዲገናኝ እያደረጉ ነው፡፡

የስም አወጣጥን በሚመለከት ከሀገራችን ክልሎች መካከል እንደጎጃም ብዙ የሚጠቀስና በስፋት የሚነገርለትም የለም፡፡ ጎጃሜዎች ስም አወጣጥ ያውቃሉ፡፡ የልጅና የአባት ስም ከአያት ጋር ተዳምሮ ድብልቅና ድርብ ዐረፍተ ነገር የሚሠሩበት ጊዜ ያጋጥማል፡፡ ‹ዓለምባንቺ ብርሃኑ ቦጋለ› የሚል ስም ከጎጃም እንጂ ከሌላ እንደማይሆን ብንጠራጠር ብዙም አንሳሳትም፡፡ በዚያ ክልል ስምን በዘፈቀደ የሚያወጡ ጥቂቶች ናቸው፡፡ ለአብነት የሚከተሉትን እውነተኛ ስሞች እንመልከት፡፡ (እኔ ከማውቃቸው መካከል ነው)

‹ሺ ማጫሽ ሺ መገመቻሽ አባይ በደጅሽ ተከዜ በጅሽ ለይኩን›፡፡ (ለይኩን የአባት ስም ነው)

‹የዋርካው ዛፍ ዛፉም ሥሩም ቅርንጫፉም ሁለመናው ዘርፍሽ አበበ ምንውየለት ለእግዚአብሔር ወረደ ወልድ›፡፡ (ወረደ ወልድ የአባት ስም ነው) ‹ዓለምባንቺ ቦጋለ ብርሃኑ ቢሆነኝ› (እስከ ቅድመ አያት የዘለቀ ስም ነው) የስም ነገር ከዚህ በላይ ይሄዳል፡፡ በአስደናቂ ታሪኮች መድብል የአንድ አሜሪካዊ ስም የፊደሎች ብዛት 101 መሆናቸውን ማንበቤ ትዝ ይለኛል፡፡ በዚህ በመከረኛ የጊነስ መዝገብ ለመመዝገብ ሲሉ አንዳንዶች የተለዬ ነገር ማድረግን ወይም ሆኖ መገኘትን ማዘውተራቸው ደግሞ ሌላው የእንግዳ ነገሮች መከሰቻ መንገድ ነው፡፡

በነገራችን ላይ ሺ ማጫሸ… በሚል የጠቀስኳት በወጣትነት ዘመኔ በሩቅ ቅርበት የማውቃት የነበረችው ወጣት ለእልኋ ‹ሺ ማጫሸ› ብላችሁ ባጭሩ ብትጠሯት አቤት አትልም - ሁሉም ስሟ ካልተጠራላት፡፡ ስለዚህ በአንድ የቀልዶች መጽሐፍ ላይ ሳነብ እንዳገኘሁት - የቀድሞውን የኢትዮጵያ መሪ ባለቤት እመት ውባንቺን ጠርታ ባለቤቷን ኮሎኔል መንግሥቱን ለምን ቡና እንደማትጠራ የተጠየቀች አንዲት ጎረቤት ‹ኧኸ፣ የሳቸውን የማዕረግና የሥልጣን ስም ሁሉ አግተልትዬ እስከምጠራ ቡናየ ይብረድብኝ?› እንዳለቺው በሙሉው ስማቸው ጥሩን ብለው ድርቅ ካሉ እነሺ ማጫሸም ባቅማቸው ቡናችንን ሊያቀዘቅዙብን ነው ማለት ነው፡፡

## ቃሪያ አዟሪው

የአንዳንድ ሰው የዋህነት ይገርማል፡፡ በቅርቡ አዲስ አበባ ውስጥ ላምበረት በሚባለው አካባቢ ቃሪያ በትከሻው ተሸክሞ እየዞረ የሚሸጥ ጎልማሣ ሰው አገኛለሁ፡፡ እንደልማድ ሆኖብኝ መንገድ ላይ የሚሸጡ ዕቃዎችን መግዛት አዘወትራለሁና - ዋጋቸው ቀነስ ስለሚያደርግ ማለት ነው - ‹ኪሎውን በስንት ነው የምትሸጠው?› ብዬ እጠይቀዋለሁ፡፡ ሰውዬውም ‹አሥራ አምስት ብር› ይለኛል፡፡ እከራከርና አንድ ኪሎውን በአሥር ብር እገዛዋለሁ፡፡ መመዘኛ ስለሌለው ግን ሚዛን የሚገኝበት ሌላ ቦታ እኔ ራሴ የላክሁት ልጅ አስመዝኖ ሲመጣና አንድ ሁለት ቃሪያ እንዲጨምርበት ሲነግረው ራሱ ይዞ ሄዶ ሲያስመዝን እንዲያውም ሰባት ቃሪያ ይጨምራል፡፡ ይሄ አይደለም የሚገርመው ነገር፡፡ ያ የላክሁት ልጅና በአካባቢው የነበሩ ሌሎቹ ወጣቶች ስለዚሁ ሰው ቀደም ሲል የታዘቡትን ሲነግሩኝ እንዲህ አሉኝ፡፡ ‹‹ይሄ ቃሪያ ሻጭ ሞኝ ነገር ነው፡፡ በቀደም ዕለት አንዲት ሴት ተሸክሞት የነበረውን ቃሪያ ሁሉ ልግዛህ ብላ በጠራላት ዋጋ ሂሳቡን አስባ ብትሰጠው ‹ሁሉን ከገዛሽኝ ምን ይዤ እዞራለሁ?› አላትና በሣቅ ገደለን፡፡›› እኔም በሰውዬው የዋህነት ተገርሜ ‹ለመሆኑ በእግሩ ግማሽ አዲስ አበባን የሚሆን ሥፍራ የሚያካልለው ቃሪያውን ለመሸጥ ነው ወይንስ እየዞረ አገር ለማየት?› አልኩና ጠየቅሁ - ራሴን፤ ማን መልስ ይሰጠኝ?

## ‹የማይረባው ተማሪ›

አንድ ጓደኛየ በቅርብ የሚያውቀውን የአንድ ሰው ገጠመኝ አጫወተኝ፡፡

በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአንድ ክፍል ውስጥ የተከሠተ እውነተኛ ታሪክ ነው፡፡ አንድ መምህር ከአንድ የክፍል ተማሪው ጋር ኮከቡ አልገጥምለት ብሎ ሣይሆን አይቀርም ያን ተማሪ ወደዚያ ክፍል በገባ በወጣ ቁጥር እንደወገብ ቅማል ጥምድ አድርጎ ይይዘዋል፡፡ ተማሪውም መድረሻ አጥቶ ይጨነቅ ገብቷል፡፡ መምህሩ የሚለው ‹አንተ የሠነፎች ሁሉ አውራ ነህ፡ የትም አትደርስም፡፡ ትምህርቱን ትተህ ይልቁንስ ከብት ብትጠብቅ ነው የሚሻልህ፡፡ አበያ…› ይለዋል፡፡ ሊያስተምር ወደክፍል በመጣ ቁጥርም ልጁ እጁን ሳያወጣ እየጠየቀ ያሸማቅቀዋል፡፡ በዚያን ጊዜ ያ ልጅ መግቢያ ቀዳዳ እየጠፋው ክፉኛ ይጨነቃል፤ይጠበባል፡፡ ምን እንደሚያደርግም ግራ ይገባዋል፡፡ ለወላጆቹም ይናገርና የተሻለ አማራጭ ሆኖ የሚያገኙት ሌላ ቦታ ሄዶ ዘመድ ቤት ተቀምጦ እንዲማር ማድረግ ይሆናል፡፡ ጊዜ ባለውሉ ሥራውን አልዘነጋም፤ እናም ይነጉዳል - ይከንፋል ቢባል ይሻላል፡፡ ያ በመምህሩ የተፈዘበት ተማሪ በከፍተኛ ማዕረግ ኮሌጅ በጥሶ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በመምህርነት ይቀጠራል፡፡

ከዕለታት አንድ ቀን ይህ የዩኒቨርስቲ መምህር የክረምት ኮርሰኞችን ሊያስተምር ክፍል ሲገባ ያ ዱሮ ‹አንት እማትረባ ውዳቂ› እያለ በነጋ በጠባ ያሰቃየው የነበረው ክፉ መምህር የትምህርት ደረጃውን ከዲፕሎማ ወደዲግሪ ለማሻሻል ፈልጎ እፊት ለፊቱ ተቀምጦ ያገኘዋል፡፡ በዳይ ረስቶታል፤ ተበዳይ ግን ቁስሉ መቼም አይጠግምና ከነመልኩና ከነሙሉ ስሙ በደንብ ያስታውሰዋል፡፡ ይህ ወጣት መምህር ወደ ክፍል ገብቶ አስተምሮ ሲጨርስ ወይም በማስተማር ላይ እያለ ጥያቄ ሲጠይቅ እንዲመልስለት ቀድሞ የሚጠይቀው ያንን ሰውዬ ይሆንና የተገላቢጦሽ ነገር ይፈጠራል፡፡ ሰውዬው ዱሮ የሠራውን ሥራና ተበዳዩን እርግፍ አድርጎ በመርሳቱ እየሆነ ያለው ነገር አልገባህ ብሎት የመምህሩን ትኩረት በዚያ መልክ መሳቡ ዘወትር ግራ ይገባዋል፤ ለጥያቄዎቹ መልስ ልስጥ ብሎ ሲሞክርም መቼስ ንፍጥ ከደረቀ በኋላ የትምህርትን ነገር ታውቁታላችሁና ጥያቄውና መልሱ እየተወላከፈበት በክፍል ጓደኞቹ ፊት ሀፍረት ቢጤ ሳያሻማቅቀው አልቀረም፡፡ የሚያደርገውን ሲያጣ መምህሩ አስተምሮ ሲወጣ ይከተለውና፤ ‹ መምህር፣ እኔን ብቻ ለይተህ ሁልጊዜ የሚከብደኝን ጥያቄ የምትጠይቀኝና በጓደኞቼ ፊት የምታሳጣኝ ለምንድን ነው? ደግሞስ ምን አጥፍቻለሁ? አባትህስ አልሆንም የኔ ልጅ!› ብሎ ይጠይቀዋል፡፡ ወጣቱ መምህርም በሃሳብ ፈረስ ወደልጅነት ጊዜው የኋሊት ሽምጥ ይጋልብና የዱሮ መምህሩ በልጅነቱ ምን ምን እንዳደረገው በማስታወስ፤‹አዩ መምህር፣ እኔንም እንዲህ ነበር የሚያደርጉኝ…› በማለት በርሱ ክፍለ ጊዜ እንዴቱን ያህል ይሰቃይ እንደነበረ ሊያብራራለት ከመጀመሩ የጊዮርጊስን ግብር የበላ እንዲሉ ‹የት? መቼ? ለመሆኑ አንተ ማን ነህ?› በሚሉ የጭንቅ ወለድ ጥያቄዎች ያጣድፈዋል፡፡ ጊዜውንና ቦታውን ከገለጠለት በኋላ ወጣቱ መምህር የክፍል ውጭ ‹ሌክቸሩ›ን እንዲህ ሲል ይቀጥላል፤ ‹…ለዚያውም ገና በለጋነት ዕድሜየ ነው፤ ችግሩን ተረዱት አይደል? ተማሪን ካለአበሳው ማሰቃየት ምን ያህል መጥፎና ውጤቱም ከሥነ ልቦና ጋር በተያያዘ ሁኔታ አደገኛ መሆኑን አሁን ተገነዘቡት አይደለም? ወቀስከኝ አይበሉኝና ያኔ ልክ አልሠሩም፡፡ ይበሉ አሁን ይቅር ብዬዎታለሁ፡፡ ለወደፊቱ ከዚህ ዱሮ ያለፈ ነገር ትምህርት ቀስመው ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈጽሙ ጥንቃቄ ያድርጉ፡፡ ከእናቱ ሆድ ተምሮ ሁሉን ነገር ዐውቆ የሚወለድ ማንም የለም፤ በጣም በድለውኛል ግን ት/ቤት ቀይሬ መማሬ ጠቀመኝ፡፡ … › በማለት ብሶቱን ገልጾ ከዚያን ቀን በኋላ በጥሩ ግንኙነት ለመበቀልም ጭራሽ ሳያስብ ማስተማሩን ቀጠለ፡፡ መጥፎ ለሠራብህ/ሽ ደግ መዋል መልካም ነው፡፡ በቀል በቀልን እየወለደ መቋጫ ለሌለው ችግር ስለሚዳርግ አለመበቀልን የመሰለ ጥሩ ነገር የለም፡፡

# ለፈገግታ ያህል

## ዕወቅ ያለው በዐርባ ቀኑ…

‹ዕወቅ ያለው ባርባ ቀኑ ያውቃል፤ አትወቅ ያለው ባርባ ዓመቱም አያውቅም› የምንለው አባባል ብዙውን ጊዜ ትክክል ነው፡፡

ካሊፎርኒያዊው አድራጎን ኢስተውድ በሰኔ 1988 በሂሣብ ትምህርት የባችለር ዲግሪውን ተቀብሏል፡፡ ኢስትውድ በውጤቱ በእጅጉ እንኳን ደስ ያለህ ሊባል የሚገባው ነው፡፡ ለዚህ ማዕረግ የበቃው በስንት ዕድሜው እንደሆነ ቢሰሙ ይደነቃሉ - በአሥራ አንድ ዓመቱ!

## ሟርተኛው ቴምብር

ከአሜሪካ የፖስታ ቴምብሮች ሁሉ በ1981 የታተመውን ያህል ከታሪካዊ ክስተት ጋር የተገጣጠመ የለም ይባላል፡፡ በዚሁ ቴምብር ላይ የተመለከተው የአውሮፕላን ሥዕል በስህተት ያላዩ ወደታች ተገልብጦ የታተመ ነበር፡፡ የፖስታውም ሆነ የማተሚያ ቤት ሠራተኞች ስህተቱን ሳያጤኑ ቴምብሩ ገበያ ላይ ዋለ፡፡ በዚያው ዕለት ቴምብሩ ላይ ምሥሏ የተቀረጸው አውሮፕላን በደረቷ ማለትም ጎማዋን ተጠቅማ ማረፍ ሲገባት በቴክኒክ ችግር ምክንያት ሜሪላንድ ውስጥ በአናቷ ተገልብጣ መሬት ላይ ዐረፈች፡፡ የሚገርም አጋጣሚ፡፡ ግዕዙ ይህን ዓይነቱን ነገር ‹ትንቢትሰ ይቀድሞ ለነገር› ይለዋል፡፡

## ሲመሽ ወደ ዱር

የካናዳ ተወላጅ የነበሩት ዴቪድ ማንትስ ይባሉ የነበሩ ሰውዬ በ72 ዓመታቸው የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎታቸውን ለማበርከት ተመዘገቡ፡፡ በ96 ዓመታቸው በእርሻ ሥራ ውስጥ ተሰማርተው በስተርጅና ይማስኑ ገቡ፡፡ በ103 ዓመት ዕድሜያቸው ያለምንም ችግር መኪና ያሽከረክሩ ነበር፡፡ በ109 ዕድሜያቸው የመጀመሪያ መጽሐፋቸውን ደርሰው አሣተሙ፡፡ በ114 ዓመታቸው በቀን ስምንት ማይል ወይም 12.8 ኪሎ ሜትር በእግራቸው ይጓዙና በሚገባ ይደንሱ ነበር፡፡ በስተርጅና ዘመን ወገብን ይዞ ማቃተትና አልጋ ላይ ተዘርሮ ሞትን መጥራት ፋይዳቢስ መሆኑን ከኚህ አረጋዊ በመማር አርአያነታቸውን እንዲከተሉ አዛውንት ዘመዶቻችንን እንምከር፡፡

## ወፍ እንዳገሯ ትጮሃለች

የሀዘን ልብስ እንደየሀገሩ ይትበሃል ይለያያል፡፡ በአንዳንድ ሀገሮች ሀዘንተኞች ሙሉ ነጭ ልብስ ይለብሳሉ፡፡ በሌሎች ደግሞ ሙሉ ጥቁር ልብስ፡፡ ጥቁሩ ልብስ መለበስ የተጀመረው ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ ጥንት ከቀብር በኋላ የሚቹ መንፈስ በቅርብ የሚያውቀውን ሰው ፈልጎ ይሰርፅበታል የሚል ዕምነት ነበር፡፡ ታዲያ ይሄው መንፈስ ‹ጥቁር ልብስ የለበሰን የቅርብ ዘመዱን ለይቶ ለማወቅ ይቸግረዋል› የሚል ዕምነት በሰዎች ዘንድ በማደሩ የሙት ወገኖች በዚሁ መንፈስ ተጠቅቶ ላለመሞት ጥቁር መልበስ እንደጀመሩ ይነገራል፡፡

## የእምነት ዕዳ

የስምንት ዓመቱ ኢጣሊያዊ ጉስቶ ዱራንቴ በቴሌቪዥን የሚተላለፈውን የአስማት ትርዒት እየተመለከተ ነበር - የዕጁ ጣቶች እርስ በርሳቸው የተቆላለፉት፡፡ ፊልሙ ሲያልቅ የዱራንቴን ዕጆች መለያየት የሚችል አንዳችም ምድራዊ ኃይል አልነበረም፡፡ ምክንያቱም የአስማተኛው ትርዒት በልጁ ላይ ተፅዕኖውን አሳድሮ ነበርና ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ለሦስት ሰዓታት ዱራንቴ ዕጆቹ ተቆላልፈው ከቆዩ በኋላ አስማተኛው ብላቴናውን በስልክ እንዲያነጋግረው ይደረጋል፡፡ አስማተኛው በስልክ የዱራንቴ ዕጆች ነጻ እንደሆኑ ከነገረው በኋላ የተሳሰሩት የዕጆቹ ጣቶች ተለያዩ፡፡ ‹ነኝ ብለህ ያመንከውን ትሆናለህ› ብሎ የተናገረው ማን ነበር?

## ፍቅር ሞገደኛው

ወንዱ ንብ አንዷን የንብ ኮረዳ በፍቅሩ ፍላፃ ወግቶ ሊያንበረክካት ሲፈልግ ልዩ መዓዛ ከየተክሉና ከየአበባው ይቃርምና ከራሱ ተፈጥሯዊ ኬሚካል ጋር በማዋሃድ ደስ የሚል ጠረን ከሰውነቱ ያመነጫል፡፡ ከዚያም ቀልቡን ወዳማለለችውና በዐይን ፍቅር አቅሉን ወዳሳተችው የንብ ልጃገረድ ይሄድና ጥያቄውን በትህትና ያቀርባል፡፡ ነገሩ እኛ ሽቶ ተቀብተን የሰውን ትኩረት ለመሳብ እንደምንሞክረው መሆኑ ነው፡፡ በተለይ ወንዶች ከዚህ የንብ ጎረምሣ የምንማረው ሌላውና ዋናው ቁም ነገር ጉልበት አለን ወይም ገንዘብና ሥልጣን አለን ብለን ጤናማ ጎሊናን ሳይሆን የአእምሮ ጡንቻን በመጠቀም ሴቶች እህቶቻችንን ማጥቃት እንደማይኖርብን ነው፡፡ አስተዋይነት የተሞላበት ብልኃትን እንጂ ድንቁርናን ደጀኑ ያደረገ ጉልበትን መጠቀሙ ላልተፈለገ አደጋ ይጋብዘናልና ለሁሉም ጥንቃቄ ይቅደም፡፡

## የተገላቢጠጦሽ

የዱሮ አንዳንድ ነገሮች ዛሬ የተገላቢጦሽ እየሆኑ ይመስላል፡፡ በዘመናችን የሕዝብ ብዛት ብዙ የዓለም መንግሥታትን ጭንቅላት እያዞረ ይገኛል፡፡ ዱሮ ሰዎች ትዳር እንዲመሠርቱና ልጅ እንዲወልዱ ይመከር ነበር፡፡ ዛሬ ግን በብዙ ሥፍራዎች ተቃራኒውን እየታዘብን ነው፤ መውለድ ያሸልም እንዳልነበር ሁሉ አለመውለድ የሚያስመሰግንበት ዘመን ላይ ደርሰናል፡፡

የአሜሪካን ግዛት በሆነችው ሚሶሪ በ1821 አካባቢ በወጣ አንድ ሕግ ዕድሜያቸው ከ21 እስከ 50 የሆኑ ወንደላጤዎች (ባለማግባታቸው ምክንያት) ለመንግሥት የአንድ ዶላር ግብር እንዲከፍሉ ይገደዱ ነበር፡፡ ዛሬ ግን ሁሉ ነገር የተገላቢጦሽ ሆነና ከጥቂት ሀገሮች በስተቀር አብዛኛዎቹ የዓለም ሀገራት በሕዝብ ብዛት በመጨናነቃቸው ትዳር ለማይዝና ለማይወልድ ሽልማት ያዘጋጁ እንደሆነ እንጂ ሰዎች እንዲያገቡ አያስገድዱም፡፡

(ምንጭ፡ ካዘና ከሚባል የሻለቃ አባይነህ አበራ የትርጉም መጽሐፍ ወቅታዊነትን ለመጠበቅ ከመጠነኛ አርትዖት ጋር የተወሰደ)

## ‹አይገርማችሁም?›

ጋብሮቮዋ ቤት እንግዶች ይመጡና ቂጣ ታቀርብላቸዋለች፡፡ እንግዶቹም አንደኛውን ቂጣ ወዲያውኑ ቅርጥፍ አደረጉት፡፡ አፈረችና ሁለተኛ ቂጣ ጋግራ ብትሰጣቸው እሱንም ቅም ሳይላቸው ጨርሰው ዐይናቸውን ማቁለጭለጭ ጀመሩ፡፡ ሁኔታው ያላማራት ሴትዮ በመገረም እያጨበጨበች ‹ እይገርማችሁም? ልክ እናንተ ስትጠግቡ ዱቄቱም አለቀ!› አለቻቸው፡፡ ጋብሮቧ ሴትዮ እውነት አላት - ታዲያ የወር አስቤዛዋን ለሁለት እምብርት ብሎ ነገር ያልፈጠረባቸው ጋብሮቮች ሰጥታ በአንድ ቀን ትጨርሰው? ለዚሁም እሷው ሆና ነው፡፡ ሊያውም በጋብሮቮች ምድር?

(ምንጭ፤ቀልዶች ከጋብሮቮች ምድር በአረፈዓይኔ ሐጎስ)

## Stop Redundancy

The Committee for the Reduction of Redundancy and the Antiproliferation of Repetition has decided not to meet until they have their first meeting and thus there won't be meeting until the first time of the first time meeting.

Their Pre-meeting Statement wanted to make this clear before they had their first meeting, so that it would not be confusing.

So their first meeting will actually be their first meeting and they will not have a meeting before the first meeting.

This should avoid having people show up for their first meeting before it is held, since to do so would be confusing to those who did so and this is what they want to avoid by reducing the confusion and lessening the repetition.

Source:http://www.ahajokes.com/eng008.html

### በመሥሪያ ቤታችን ያለው የኮሚቴ ብዛት.....

በደርግ ዘመነ መንግሥት ነው፡፡ በአንድ መሥሪያ ቤት ውስጥ የኮሚቴ መዋቅር በዝቷል የሚል ጥቆማ ለሥራ አሥኪያጁ ይደርሳል፡፡ ይሄ ሰውዬ የሥራ ኃላፊዎችን ወዲያውኑ ስብሰባ ይጠራና ‹ጓዶች በመሥሪያ ቤታችን የኮሚቴ ብዛት ከመጠን እንዳለፈ ተነግሮኛል፡፡ ስለዚህ ይህን ሁኔታ አጥንተው ሪፖርት የሚያደርጉ አንድ ሁለት አዳዲስ ኮሚቴዎችን አሁኑኑ እናቋቁምና ወደሥራው ይግቡ፡፡› አለ ይባላል፡፡ ከላይኛው ጋር አይመሳሰልም?

### መምህር ሊቁ

ወትሮም ሻማ አይሆን ለሱ፤
        የሌሎች ናት ሥጋ ነፍሱ፤
ላገር ደምቆ እዬበራ፤
        ጥበብ ሸማን እዬሠራ፤
ቋሚ ሰንደቅ አስቀምጦ፤
        እሱ ያልቃል ነዶ ቀልጦ፡፡
የፊደል ዘር እዬዘራ፤
        የ'ውቀትን ውል እያደራ፤
የታሪክ ሰው ባላደራ፤
        መምህር ሊቁ የሰው አውራ፤
የዘመን ጧፍ ሆኖ በራ፡፡
        ጠመኔ ጦር ብዕር መድፉ፤
ያገር ክብር ፀጋ ትርፉ፤
        ፀሐይ ብርሃን ቀንዲል ጮራ፤
ቤዛ ሆነ ገድል ሠራ፤
        መምህር ሊቁ የሙያ አውራ፡፡
ብርሃን ችቦ እያነደደ፤
        ድንቁርናን እዬናደ፤
ፋና ወጋ ደምቆ በራ፤
        ቤዛ ሆነ ጥበብ ሠራ፤
መምህር ሊቁ ያር አውራ፡፡

ውዳላት ገዳሙ፤ ‹እናትና ልጅ› የግጥም መድብል፤1996ዓ.

## Some School Jokes

### The ways to grade the final exams

Dept of Statistics:

All grades are plotted along the normal bell curve.

Dept of Psychology:

Students are asked to blot ink in their exam books, close them and turn them in. The professor opens the books and assigns the first grade that comes to mind.

Dept of History:

All students get the same grade they got last year.

Dept of Religion:

Grade is determined by God.

Dept of Philosophy:

What is a grade?

Law School:

Students are asked to defend their position of why they should receive an A.

Dept of Logic:

If and only if the student is present for the final and the student has accumulated a passing grade then the student will receive an A else the student will not receive an A.

Dept of Computer Science:

Random number generator determines grade.

Music Department:

Each student must figure out his grade by listening to the instructor play the corresponding note (+ and - would be sharp and flat respectively).

Dept of Physical Education:

Everybody gets an A.

Teacher: In 1940, what were the Poles doing in Russia?
Pupil: Holding up the telegraph lines!

Young Larry stopped by the corner grocery store and read the following list to the clerk:

10 pounds sugar at $1.25 a pound
4 pounds coffee at $1.50 a pound
2 pounds butter at $1.10 a pound
2 bars soap at $.83 each

"How much does that come to?" asked Larry.
"Twenty-two dollars and thirty-six cents."

"If I gave you three ten dollar bills, how much change would I get?" said the boy.

"Seven dollars and sixty-four cents," stated the clerk who appeared to be irritated by all the questions. Larry said, as he disappeared through the door, "I don't want to buy the items...that's our arithmetic lesson for tomorrow, and I needed some help with it."

* * *

**Teacher**: How many books have you read in your lifetime?
**Pupil**: I don't know. I'm not dead yet.

**Pupil**: I didn't do my homework because I lost my memory.
**Teacher**: When did this start?
**Pupil**: When did what start?

**Pupil**: This egg is bad.
**Cook**: Don't blame me I only laid the table!

**Father:** How were the exam questions?
**Son**: Easy.
**Father**: Then why look so unhappy ?
**Son**: The questions didn't give me any trouble, but the answers did!

**Father**: How did your exams go?
**Son:** I got nearly 100 in every subject.
**Father**: What do you mean, nearly 100?
**Son**: I was just a digit out; I averaged 10!

**Pupil**: I don't think I deserved zero on this test.
**Teacher**: I agree, but that's the lowest mark I could give you !

**Father:** Why did you get such a low score in that test ?
**Son**: Absence.
**Father:** You were absent on the day of the test ?
**Son**: No, but the boy who sits next to me was!

Source:http://schooljokes.informationresourcenetwork.com/index.php

# ልብ ወለድ

## አሣባቂው ልብ

**ደራሲ ፣** ኤድጋር አለን ፖ(Edgar Allen Poe)
**ትርጉም፣** ሙሉዓለም ደንበኛ
የልቦለዱ ርዕስ፤The Tell-Tale Heart (አጭር ልቦለድ)

ውነት ነው! ያልተረጋጋሁ ነኝ:: ግን ለምን ዕብድ ነው ትሉኛላችሁ? አለመረጋጋቱ የስሜት ሕዋሳቴን ይበልጥ ንቁ አደረጋቸው ንጂ አላደነዘዛቸውም:: ይበልጥ ደግሞ የመስማት ችሎ ዬ ጅግ ፈጣን ነው:: በሰማይ ና በምድር የሚነገሩትን ነገሮች ሁሉ ሰማለሁ:: ገሀነም ውስጥ የሚወራውን ወሬ ሳይቀር አዳምጣለሁ:: ዲያ ኔ ዕብድ ልባል ችላለሁ? ልብ በሉ! ሁሉንም ሪክ አንድ በአንድ ንዴት አቀለጣጥፌ መናገር ንደምችል አስተ ውሉ::

ሃሳቡ በመጀመሪያ ደረጃ አ ምሮዬ ውስጥ ንዴት ንደገባ ለመግለጽ ያስቸግረኛል:: ግን አንዴ በአዕምሮዬ ከተጸነሰ በኋላ ይኸው እስከ ዛሬ ቀን ከሌት ያሳድደኛል:: ሃሳቡ ምንም ዓይነት ዓላማ ወይም የተጨበጠ ነገር የለውም:: ሽማግሌውን በጣም ወደዋለሁ:: አሳዝኖኝ ወይም አስቀይሞኝ አያውቅም:: የዘለፋ ቃል ፈጽሞ በ ኔ ላይ አይወጣውም:: ኔም ሀብቱ አጓጉቶኝ አያውቅም:: ዐይኖቹ ግን የተለዩ ነበሩ:: አንዱ ዐይኑ በተለይ የሚንቀለቀል ሳት የሚተፋ ደብዛዛ አረንጓዴ የጆፌ አሞራ ዐይን ይመስላል:: ዐይኑ ኔ ላይ ሲያርፍ ደሜ ይረጋል:: ለዚህም ነው ቀስ በቀስ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሽማግሌውን ገድዬ ከ ነዛ አስፈሪ ዐይኖች እስከወዲያኛው ለመገላገል የወሰንኩት::

ንግዲህ ነገሩ ንዲህ ነው:: ንክ ነው ብላችሁ ልትገምቱ ትችላላችሁ:: ዕብዶች ስለምንም ነገር አያውቁም:: ኔን ግን ውስጤን ብ ዩ ዕብድ ነው ብላችሁ ለመናገር አትደፍሩም ነበር:: ጉዳዩን ንዴት በብልጠት፣ በዘዴ፣ በጥንቃቄ ና በማስተዋል ንደፈጸምኩት ብ ውቁ ቀውስ አትሉኝም ነበር:: ሥራ ቀርቼ አላውቅም! ሽማግሌውን በገደልኩበት ሳምንት ደግ ንደሆንኩለት መቼም ደግ ሆኜለት አላውቅም:: ማ ማ ኩለ ሌሊት ገደማ ዘወትር በዝግ የሽማግሌውን በር ከፍትና ምንም ብርሃን የማይረጭ ፋኖስ አስቀድሜ ጭንቅላቴን አስከትዬ ወደ ክፍሉ ገባለሁ:: ጭንቅላቴን ንዴት በብልጠት አስግጌ ንደምገባ ብ ዩ ጅግ ትደነቃላችሁ:: ሽማግሌውን ንዳልቀሰቅሰው ጅግ በዝግ ቀስ ብዬ ነበር የምንቀሳቀሰው:: ሙሉ ለሙሉ አንገቴን በበሩ አስግጌ ለማስገባት አንድ ድፍን ሰዓት ይፈጅብኛል:: ጉድ ነው ጃል! ይ ያችሁ አንድ ዕብድ ሰው ንዲህ ብልህ ሊሆን ይችላል? አንገቴን በበሩ ካስገባሁ በኋላ ጅግ በዝግ የፋኖሱ ጀ ንዳይንቋቋ የተጠነቀቅኩ ከፍተዋለሁ:: ከዛም ትንሽ የብርሃን ጨረር በሽማግሌው የጆፌ አሞራ መሰል ዓይኖች ላይ ንዲያርፍ አደርጋለሁ::

ይህን ለሰባት ተከ ይ ሌሊት አደረኩኝ:: በ ነዚህ ሌሊቶች ሁሉ የሽማግሌው አስፈሪ ዐይኖች ንደተ ከደኑ ነበር:: ይኸውም ጉዳዮን በፍጥነት ንዳልፈጽም ዕንቅፋት ሆነብኝ:: የሚያስጨንቀኝ ሽማግሌው ሳይሆን ነዛ የዲያቢሎስ ዐይኖቹ ነበሩ:: ናም ጧት ጧት ጎህ ሲቀድ ወደ ሽማግሌው ክፍል ሳልሳቀቅ ገብቼ ዘና ብዬ አዋራዋለሁ:: ሌሊቱን ንዴት ንዳሳለፈ ጠይቀዋለሁ:: ሽማግሌው ቆቅ ነበር:: ሁሌ ሌሊት ስድስት ሰዓት ገደማ የሆነ ሰው በተኛ በት እያጮለቀ ንደሚያየው ጥርጣሬ ያለው መሆኑን ነገረኝ::

በስምንተኛው ሌሊት የሽማግሌውን በር ስከፍት ከበፊቱ የበለጠ ጠንቃቃ ነበርኩ:: ከ ኔ ጆች በበለጠ የሰዓት ጠቋሚ ዘንጎች ይፈጥኑ ነበር ብል ማጋነን አይሆንብኝም:: ንደዛች ሌሊት ብልጠቴና ጥንቃቄዬ ውቶኝ አያውቅም:: የድል አድራጊነት ስሜቴን መቆጣጠር አቃተኝ:: በተለይ ሼባው በህልሙ ንኳን ሥራዬን ማየት ንደማይችል ስረዳ የጀግንነት ስሜት ተሰማኝ:: ሽማግሌው ይህን ሀሳቤን የሰማ ይመስል ገልበጥ አለ:: ይባስ ብሎ ተነስቶ ቁጭ አይል መሰላችሁ? የደነገጥኩ ሊመስላችሁ ይችላል:: ግን ቅንጣት ህል አልፈራሁም:: ክፍሉ በድቅድቅ ጨለማ ስለተዋጠ የገሃነም ያህል ጥቁር ነበር:: በተለይ ሽማግሌው ሌ ቦችን በመፍራት የመስኮቱን ሻተሮች ስለሚዘጋቸው በዚያም ምክንያት ጨለማው ጅግ ስለሚገዝፍ ንደማያየኝ አውቅ ነበር:: ስለዚህ በድፍረት ቀስ ብዬ ወደ አልጋው ተ ጠጋሁ::

ቀስ ብዬ የፋኖሱን መዝጊያ ልከፍት ስሞክር አውራ ጣቴ ቦ ውን ስቶ «ቋ» የሚል ድምጽ አሰማ:: ሼ ባው ከአልጋው ላይ ተስፈንጥሮ በመነሳት «ማነው?!» ብሎ ጮኸ:: ትንፋሼን ውጬ ባለሁበት ቀጥ ብዬ ቆምኩኝ:: ለአንድ ሰዓት ያክል ዛው ውልፊት ሳልል እንደጅብራ ቀጥ ብዬ ንደቆምኩ ቆየሁ:: ተመልሶ ሲጋደም አልሰማሁትም:: ሱም ድምጽ ለመስማት በመጠበቅ በተጠንቀቅ ቁጭ ብሏል::

አሁን ቀጭን የሚጓራት ድምጽ ሰማሁ:: ማቃሰቱ ከከፍተኛ የፍርሃት ስሜት የመነጨ ነበር:: የህመምፈጽሞ ያን ዓይነት ዓይደለም! ማቃሰቱ ነፍስ በከባድ ፍርሐት ስትጨነቅ የሚወጣ ቀጭንና የ ፈነ ድምጽ ነው:ይህን የማቃሰት ድምጽ ኔ ራሴ ጠንቅቄ ዐውቀዋለሁ:: ብዙ

ሌሊት ዓለሙ ሁሉ ጧ! ብሎ በተኛ በት ወቅት ይህ ድምጽ በውስጤ ያስተጋባ ከአንጀቴ ይወጣ ነበር:: ስለዚህ የሼባው ስሜት ለ ኔም ተ ሰምቶኛል:: አዘንኩለት:: የፋኖሷን ቋቋ ከሰማበት ሰዓት አንስቶ ንዳልተኛ ዐውቄያለሁ:: ፍርሀቱ ከደቂቃ ወደ ደቂቃ የጨመረ ነበር:: ምናልባት ለራሱ «የቋቋ ው ድምጽ የተፈጠረው የቤቱን ጭስ ማውጫ ንፋስ እያቅጨለጨለው ወይም አይጥ በወለሉ ላይ ስትሄድ የተፈጠረው ኳኳታ ወይም የክሪኬት መጫወቻ ዱላ ወድቆ ሊሆን ይችላል» ያለ ያስብ ይሆናል:: ይህን ና ይህን የመሰለውን በማሰብ ራሱን ለማረጋጋት እየሞከረም ይሆናል:: ግን አልሆነለትም:: ምክንያቱም የሞት አስፈሪ ጥላ ሊውጠው ፊቱ ቆሞ ነበር:: ምንም ንኳ ባያየኝም ወይም ባይሰማኝም የማይዳሰሰው የሞት ጥላ ኔ ክፍሉ ውስጥ ንዳለሁ ንዲጠረጥር ሳያደርገው አልቀረም::

ረጅም ሰዓት በትዕግስት ከጠበቅሁ በኋላ ቀስ ያልኩ የፋኖሱን በር ከፈትኩት:: አ ምኑኝ ይሆናል ግን ከሸረሪት ድር የቀጠነች ትንሽ ጨ ረር ከፋኖሱ ተፈትልካ ወጥ ሽማግሌው የጆፌ አሞራ ዐይን ላይ ዐ ረፈች::

ያ አስፈሪ ዓይን በፍርሀት ተ በለጠጠ:: ሳየው ይበልጥ ደነገጥኩ:: ያ ጥቁር ሰማያዊ ዐይን ቁልጭ ብሎ የኝ:: አጥንቴ መቅኒ ውስጥ ፍርሀት ሲረጭ ይሰማኛል:: የፋኖሱን ጨ ረሮች ሳይ ሰበኝ ያሳረፍኩት በዛ በተ ረገመ ዐይን ላይ ስለነበር የተቀረው የሽማግሌው ፊት ወይም ሰውነት አይ የኝም ነበር::

በ ጅግ ድንጉጥነቴ ምክንያት ዕብድ ነው ልትሉኝ ትችላላችሁ ብዬም አልነበር? አዎ አሁን ደግሞ ልክ በጥጥ የ ፈነ የሰዓት ቆጣሪ የመሰለ ቀጭን ፈጣን ድምጽ ይሰማኝ ጀመር:: ይኸንንም ድምጽ ዐውቀዋለሁ:: የሽማግሌው የልብ ምት ነበር:: ድምጹ ወ ደርን ንደሚያበረ የ ምቡር ድምጽ አጀገነኝ::

ግን አሁንም ሳልንቀሳቀስ ቀስ ብዬ ቆምኩ:: ትንፋሼን ዋጥኩ:: ፋኖሱን ባለበት አቆምኩት:: በተቻ ለኝም ጨረሮቹ ከዛ አስፈሪ ዐይን ላይ ንዳይነሱ ጥንቃቄ አደርግ ጀመር:: በዛው መጠን የሽማግሌው የልብ ምት የጎላ መጣ:: የፈጠነ ... የጎላ... የጮኸ ሄደ:: የሽማግሌው ፍርሀት ከቁጥጥር ውጭ መሆን ነበረበት:: ቅድሙኑ ደንጋጣ ንደነበርኩ ነግሬያችኋለሁ:: በዛ አስፈሪ ጸጥ ከዛ ያረጀ ቤት ውስጥ በ ኩለ ሌሊት የሚሰማው ድምጽ ፍርሀቴን አባሰው:: አሁንም ግን ቅስቅስ ወይ ትንፍሽ አላልኩም:: የሽማግሌው የልብ ምት ግን የጨመረ የጎላ... የጨመ ረ... የጎላ... ሄደ:: ልቡ ሊፈነዳ የደረሰ መሰለኝ:: አሁን ደግሞ ሌላ ጭንቀት ያዘኝ:: የሽማግሌው የልብ ምት ጎረቤ ት ይሰማ ይሆን?! ሰዓቷ ደረሰች:: የጮኽኩ የፋኖሱን መዝጊያ ሙሉ ለሙሉ ከፈትኩት:: ዘልዬ ወደ ክፍሉ ውስጥ ገባሁ:: አንድ ጊዜ ብቻ በቀጭኑ ጮኸ:: ከአልጋው አውርጄ አልጋውን በላዩ ላይ ጫንኩበት:: የልብ ምቱ ግን ንደ ፈነ ለረጅም ደቂቃ ቆየ:: በዚህ ብዙም አልተ ደናገጥኩም:: ምክንያቱም ይህ ድምጽ ግድግዳውን ጥሶ ለጎረቤት ሊሰማ አይችልም:: በመጨረሻ ሁሉም ነገር ፀጥ አለ:: ሽማግሌው ለዘለዓለሙ አንቀላፋ:: አልጋውን ከላዩ ላይ አንስቼ ሬሳውን ተመለከትኩት:: ጄን ደረቱ ላይ ጭኜ ለረጅም ደቂቃዎች ቆየሁ:: ምንም የልብ ምት የለም:: ሽማግሌው ሞቷል:: ከአሁን ጀምሮ ያ አስፈሪ ዐይኑ አያስጨንቀኝም::

አሁንም ዕብድ ነው ብላችሁ የም ስቡ ከሆነ የሽማግሌውን ሬሳ ለመደበቅ ያደረኩትን ጥንቃቄ ስገልጽላችሁ ይህን አስተሳሰባችሁን ትሠርዙታላችሁ:: ሌሊቱ የተገባደደ ስለነበር መፍጠን ነበረብኝ:: ግን በፀጥ :: በመጀመሪያ ሬሳውን ከተ ከትኩት:: የሼባውን በድን፡- ጭንቅላት፣ ዕጆች ና ግሮች ሁሉንም ለበዓል እንደታረደች የዶሮ ብልት ቆራረጥኳቸው::

የወለሉን ሳንቃ አንስቼ ሁሉንም የሽማግሌውን ቁርጥራጮች ከሳንቃው ሥር አኖርኳቸው:: ከዛ ቀስ ብዬ በዘዴ የዕቃ ቁም ሣጥኑን በሳንቃው ላይ ጫንኩበት:: ምንም የሚ ጠብ ወይም የሚፀዳ ደም ነጠብጣብ በአካባቢው አልነበረም:: ሁሉንም ነገር በቁጥጥር ሥር አዋልኩት::

ይህን ሁሉ አድካሚ ሥራ ስጨርስ ሰዓቱ ከሌሊቱ አሥር ሰዓት ገደማ ነበር:: አሁንም ጨለማው ድቅድቅ ብሏል:: የሰዓቱ የደወል ዕጀታ ጊዜው ከሌሊቱ ልክ አሥር ሰዓት መሆኑን ሊያውጅ ድንገት ባላሰብኩበት ሁኔታ ሲያንቃጭል የ ችኛው በር ተንኳኳ:: አሁን ምንም የሚያስፈራኝ ነገር ስላልነበረ ዘና ብዬ ሄጄ በሩን ከፈትኩት፤ ምክንያቱም የልቤ ሃሳብ ሞልቷል! ሦስት ፖሊሶች በሩ ላይ ቆመዋል - ለምን መቶ አይሆኑም፤ ብያዝ ባልያዝ አሁን ግዴለኝም:: ለካስ አንድ ጎረቤት የሽማግሌውን ቀጭን የስቃይ ጩኸት ሰምቶ ሁኔ ውን ለፖሊስ አሳውቋል:: ፖሊሶቹም ቤቱን ለመፈተሽ ሥልጣን ንደተሰጣቸው ከነገሩኝ በኋላ ወደ ውስጥ ገቡ::

ፈገግ አልኩኝ:: ምን ያስፈራኛ ል? ፖሊሶቹን ሰላም ካልኳቸው በኋላ ወደ ውስጥ ንዲዘልቁ ጋበዝኳቸው:: ቀጭኑ ጩኸት በህልሜ ስቃዥ ያሰማሁት ንደሆነ ና ሽማግሌው ከአገር ከጠፋ ንደቆየ ለፖሊሶቹ ለማስረዳት ሞከርኩ:: መኮንኖቹን ሁሉንም የቤቱን ክፍል ያዘዋወርኩ አስጎበኘኋቸው:: በደንብ ቤቱን ንዲፈትሹ ና ንዲያስሱም ፈቀድኩላቸው:: ሰውዬውንም ወደቀበርኩት ቦ ሳይቀር ወሰድኳቸው:: ሀብቱን፣ ንብረቱን ምንም ሳልረበሽ አሳየኋቸው:: ወንበር አምጥቼ ከድካማቸው ትንሽ ዐረፍ ንዲሉ ጋበዝኳቸው:: ኔም በድል አድራጊነት ስሜት ልክ ሽማግሌውን የቀበርኩበት ቦ ወንበር አምጥጩ ተመቻችቼ ተቀመጥኩ::

የፖሊስ መኮንኖቹ ባደረጉት ፍተሻ ረኩ:: ሁኔ ዬ ና አቀባበሌ አሳመናቸው:: ፍጹም መረጋጋት ይ ይብኝ ነበር:: ከጎኔ ቁጭ ብለው ያወጉ ጀመር:: ጥቂት ሳይቆይ ግን ፊቴ መገርጣት ጀመረ:: ቶሎ ንዲሄዱ ተመኘሁ:: ጭንቅላቴን ይፈልጠኝ ጀመር:: ጭው የሚል ድምጽ የሰማሁ መሰለኝ:: ሆኖም ግን

ወደ ገጽ 63 ዞረሯል

# ዳሰሳ

## መምህር ያጣመመውን ማንም አያቃናውም

ታምራት ኃይሌ

በሥነ ልቦና የትምህርት ዘርፍ ይበልጥ አግባብነት ሊኖረው ይችላል ብዬ የምገምተው የአንድ ጥያቄ መልስ አለ፡፡ ጥያቄው በአንድ ብርጭቆ ውስጥ የሚገኝን የውኃ መጠን ስለመናገር የሚመለከት ነው፡፡ አንዳንዶች ሲመልሱ ‹ ብርጭቆው ግማሹ ድረስ ሙሉ ነው› ሊሉ ይችላሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ‹ብርጭቆው ግማሹ ድረስ ባዶ ነው› ብለው ሊመለሱ ይችላሉ፡፡ መልሱ የሁሉም ተመሳሳይ ነው፡፡ ነገር ግን መልሱን አዳማጩና መልሱን መላሾቹ ምን ዓይነት ሥነ ልቦናዊ ቀመር እንዳላቸው የምናውቅበት አንድምታዊ ሥሌት በመልሶቹ ውስጥ ተሰንቅሮ ይገኛል፡፡

ችግሩ የቋንቋ አይደለም፤ የአመለካከት እንጂ፡፡ ግማሽ ሙሉ ያለው ለሕይወት ያለው ግምት አወንታዊ እንደሆነና ግማሽ ባዶ ያለው ደግሞ ለነገሮች ምን ያህል ጨፍጋጋ አመለካከት እንዳለው ያሳያል ይላሉ የሙያው ጠበብት፤ መልሱን እሚያዳምጠው ሰው በመልሶቹ ላይ ተመርኩዞ በተጠያቂዎቹ ላይ የሚኖረው የራሱ ግምት ይኖራል፡፡ ይህ ሁሉ ‹ፍልስፍና› የቀደመው አለነገር አይደለም፡፡ ይህን ጽሑፍ ልጫጭር ስነሳ ከየትኛው ልጀምር ብዬ በተወሰነ ደረጃ ከራሴው ጋር ተሟግቻለሁ፡፡ ‹ጥሩ መምህር እንዴት ያለ ነው?› ብዬ ልነሣ ወይንስ ‹መጥፎ መምህር እንዴት ያለው ነው?› ከሚለው ልጀምር ብዬ ትንሽ አሰብ አደረግሁ፡፡ በሁሉም አቅጣጫ ብነጉድ መዳረሻየ አንድ መሆኑን ስረዳ ባሻኝ ብጀምር ምንም ማለት እንዳልሆነ ገባኝና በዚህ ረገድ ጊዜ ላለማጥፋት፣ ላለመጨነቅም ወሰንኩ፡፡ እናም አእምሮየ እንደመራኝ በተነሣሁበት የመምህራን ጥሩም ይሁን መጥፎ ጉዳይ የብዕር ፈረሴን ኮልኩዬ ቼ በለው ልል ነውና በታሪኮቹ የተካተታችሁም ያልተካተታችሁም በትዕግሥት ተከታተሉኝ፡፡ ስሞች በአጋጣሚ ቢመሳሰሉ እንጂ በክፋት ወይም በሸር ሆን ብዬ እንዳላደረግሁ እዚችው አሁን ተረዱልኝ፡፡

ይህ ጽሑፍ ጥናታዊ አይደለም፡፡ በተጨባጭ የጥናትና ምርምር መረጃዎች የተደገፈ አይደለም፡፡ እንደማንኛውም ከሕይወት ወንዝ የተጨለፈ የምድራዊ ኑሮ ተሞክሮ ሊወሰድና ለቀጣይ የጥናት ዘገባዎች በጥሬ መረጃነት ሊያገለግል ግን ይችላል፡፡ ጥናታዊ ጽሑፍ አይደለም ሲባልም የሚነሱት ፍሬ ሃሳቦች ልቦለዶች ወይም መላምታዊ ናቸው ለማለት እንዳልሆነ መግለጽ እፈልጋለሁ፡፡ ይህ ጽሑፍ በየትኛውም የትምህርት ደረጃ ለሚያስተምሩ በተለይ ለወጣት መምህራን የሚጠቅም ግብኣት እንደሚኖረው ‹ጸሐፊ›ው በብርቱው ያምናል፡፡ የሕይወት ወንዝ የዋዛ አይደለችም፡፡ ብልጥኖች ብዙ ይቀዱባታል(‹ቀ›ን ላላ አድርጉና አንብቡልኝ)፤ ሞኞችና ሠነፎች ግን ዕድሜ ልካቸውን በንቀት፣ በትዕቢትና በትምክህት ባሕር እዬዋኙ ራሳቸው በፈጠሯት ጠባብና ዝግ የቅዠት ወይም የሞኝነት ዓለምም እየተናጡ መቅዳት የሚገባቸውን ያህል ሳይቀዱ ከጉዟቸው ተሰናክለው ይቀራሉ አለዚያም ዕድሜያቸውን ሙሉ ተንዘላዝለው ሞት መቼም ለማንም አይቀርምና እነሱም ለወጉ ያህል ይሞታሉ፡፡ ስለዚህም ወጣቶች ከዚህች ማዕድ በሚያገኟት የሌሎች ሰዎች የረዢም ሕይወት ተሞክሮ መስታዎትነት የራሳቸውን የአሁንና የወደፊት ሕይወት ከተመሳሳይ የቆሸሸና በዕኩይ ምግባር የጨቀዬ ስብዕና ነጻ እንዲያወጡ ይመከራሉ፡፡ ‹ምክር የድኻ ነበርሽ ማን ቢሰማሽ› እንደተባለው እንዳይሆን እንጂ ‹እህ… እስኪ በል ንገረኝማ› ብሎ ጆሮውን ለቁም ነገር የሚያውስ አስተዋይና ጥበበኛ አድማጭ ከየትኛውም አቅጣጫ ከሚወረወሩ ፍካሬ ቃላት የሚሸምተው ብዙ ፍሬ ነገር አያጣም፡፡

መምህር ምንድነው? በሚለው ለዚህ ጽሑፍ መሠረታዊ ሊሆን በሚችል ጥያቄ እንጀምር፡፡ ከቃላት አጠቃቀም አንጻር ‹መምህር› ማለት ‹መሀረ› ከሚለው የግዕዝ ቃል የመጣ እንደሆነና ትርጓሜውም ‹አስተማረ› ማለት እንደሆነ የግዕዝ ሊቃውንት ይገልጻሉ፡፡ ክርስቶስ በመጽሐፍ ቅዱስ ለደቀ መዛሙርቱ - ‹ሁሩ ወመሀሩ ውስተ ኩሉ አጽናፈ ምድር› እንዳለ፡፡ (ወደ ዓለም ሂዱና አስተምሩ) ግዕዝና አማርኛ በፆታ ረገድ መጠነኛ ልዩነት ስላላቸው ለወንድ በነጠላው ‹መምህር›፣ ሲበዛ ደግሞ ‹መምህራን› ሲል ለሴት በነጠላው ‹መምህርት› ሲበዛ ‹መምህራት› ይላል፡፡ በሌላም በኩል በሆሄያት ደረጃ ራሱ በግዕዝና በአማርኛ ልብ ሊባሉ የሚገባቸው የአጠቃቀም ልዩነቶች መኖራቸውን ያጤኗል፡፡ ለምሣሌ ከፍ ሲል በገለጽነው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ‹ሁሩ ወመሀሩ ውስተ ኩሉ አጽናፈ ምድር› የሚለውን ‹ሁሩ ወመሐሩ ውስተ ኩሉ አጽናፈ ምድር› ተብሎ ቢጻፍ ለግዕዝ መምህር ግርታን ይፈጥራል፡፡ ምክንያቱም በግዕዝ ‹መሀረ› አስተማረ ሲሆን ‹መሐረ› ሲል ምሕረትን ወይም ይቅርታን አደረገ ማለት ነውና፤ ምሕረትን የሚሰጥ ደግሞ ፈጣሪ ነው፡፡ (እርግጥ ነው ‹ምን ዓይነት ምሕረት?› የሚለው ሊያነጋግር ይችላል፤ ምክንያቱም በፈረንጅኛው ‹Salvation, Redemption, Mercy, Forgiveness, Pardon, Excuse…› የሚሉት ቃላት ያላቸው ሃይማኖታዊና ሰውኛ አንድምታ ባማርኛው ሁሉም በይቅርታነት ስለሚተረጎሙ)፡፡ እናም የሁለተኛውን አገላለጽ ለመጀመሪያው ብናውለው ትርጉሙ ‹ወደ ዓለም ሂዱና ምሕረትን አድርጉ› እንደማለት ይሆንና የትርጉም መፋለስ ያስከትላል - እንደወግ አጥባቂው ሥነ ልሣናዊ አካሄድ፡፡ በተመሳሳይ መንገድ ‹ሰረቀ› ብንልና ‹ሠረቀ› ብንል ከአነባበብ ጀምሮ እስከ ትርጓሜ ድረስ ልዩነት አላቸው፡፡ የመጀመሪያው ‹መነተፈ፣ በዘዴ ቀማ፣ሰረቀ ፣ቀጠፈ› ማለት ሲሆን ሁለተኛው ‹ወጣ› ማለት ነው፡፡ ‹ሠረቀ ለነ እምኔኪ ፀሐየ ጽድቅ ወአቅረበነ ታህተ ክነፊሁ›( ከአንቺ [ከቅ. ማርያም] በመንፈስ ቅዱስ ሥራ

በፀሐይ የሚመሰል የዓለም ንጉሥ ክርስቶስ ወጣልን(ተወለደልን)...) እንዲል ውዳሴ ማርያም ዘዐርብ፡፡ በነገራችን ላይ በዚህ ጽሑፍ የወንድ አጠራሩን ወስጄ ‹መምህር/ራን› የምል መሆኔን በትህትና ላስገነዝብ እወዳለሁ፤ ምርጫየም አጋጣሚ እንጂ ምክንያታዊ አይደለም፡፡

ወደሃይማኖት መጠጋት ሳያስፈልገን እንዲሁ በደምሰሳሳው የመምህርን ምንነት ብናይ ብዙ ማለት እንችላለን፡፤ አንድ መምህር ምን ምን መልካም ባሕርያት እንዲኖሩት ይጠበቅበታል? ማንኛውንም የትምህርትና የሥልጠና ዓይነት የሚያስተምር መምህር ወደዚህ ከዕንቁና አልማዝ በላይ ሊከበር የሚገባው ሙያ ከመግባቱ በፊት በምን የማጣሪያ ወንፊት ማለፍ ይጠበቅበታል? አንድ መምህር ትውልድን እንዲቀርጽ ወደሙያ መስኩ ከመግባቱ አስቀድሞ በምን የትምህርትና ሥልጠና የብቃት ደረጃ መለያ እርከኖች ማለፍ አለበት? የአንድ መምህር የአጠቃላይ ግንዛቤ ወይም ዕውቀት የልኬት መጠን(Intelligence Quotient - IQ)፣ የስሜታዊነቱ (ግልፍተኝነቱ?) የልኬት መጠን(Emotional Quotient - EQ) እና የመንፈሳዊ ልሂቅነቱ የልኬት መጠን (Spiritual Quotient - SQ) በአማካይ ምን ያህል ሲሆን ወይም ቢሆን ነው ወደዚህ ትውልድን የማነጽ ክቡር ሙያ እንዲገባ የሚፈቀድለት? በጣም ብዙ ጥያቄዎችን እያከታተሉ ማዥጎድጎድ ይቻላል፡፡ ለነዚህና ለሌሎች መሰል ጥያቄዎች የምንሰጠው መልስ አጥጋቢነት በትውልድ ቀረጻው ሂደት የራሱ የሆነ ወሳኝ ድርሻ ይኖረዋል - እንደትውልድና እንደሀገር በመኖርና ባለመኖር ወሳኝ ጉዳይ ዙሪያ የተቀነበበ፡፡

ሠለጠነ በሚባለው ዓለም የመምህርነት ሙያ በሮቹን ከፍቶ ተሣፋሪዎችን እንደሚጠብቅ ባቡር ወይም የከተማ አውቶቡስ ዘልለው የሚገቡበት ሣይሆን ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ የተመረጡ ጥቂቶች ብቻ የሚቀላቀሉት እንደሆነ እንሰማለን፡፡ ምክንያታቸው ግልፅ ነው፡፡ ይሄውም የአንድ መምህር ሙያ በተለይ በታችኛው የስብዕና ቀረጻ ሂደት (በፈረንጅ አፍ ‹ሥልጡናኑ› Formative Age በሚሉት) የአንድን ማኅበረሰብ መፃኢ ዕድል እስከመወሰን በሚደርስ መልኩ የወሳኝነት ሚና ስለሚጫወት አደጉ የሚባሉት ሀገሮች ይህን ሙያ ለማንም ዋልጌና ኃላፊነት የማይሰማው ወለፈንዴ ዜጋ ለቀው ትውልዳቸውን አያበላሹም - የመምህርን ማኅበረሰብኣዊ ወሳኝ ሚና ጠንቅቀው ይረዳሉና፡፡ ሥነ ልቦናዊ ዝንባሌው ተጠንቶ፣ መምህር ለመሆን ያለው ቁርጠኛ ፍላጎትና ሙያውን ከተማሪዎቹ ጋር አጣምሮ የሚወድ መሆኑ ተለክቶ፣ አካላዊ፣ ሥነ ልቦናዊና መንፈሳዊ ጤንነቱ ተፈትሾ፣ በሚያስተምረው የትምህርት ዘርፍ በቂ ሥልጠናና ልም(ም)ድ አግኝቶ፣ ሁለንተናዊ ብቃቱ በባለሙያዎች ሲረጋገጥ ብቻ ወደ ማስተማር ተግባሩ እንደሚሠማራ ይነገራል፡፡ ባላደጉ ሀገሮች ግን ብዙ መሰናክሎች ስላሉ ይህ ክቡር ሙያ የራሱን ሰዎች ስለማግኘቱ ያጠራጥራል፡፡ በአንዳንድ ሀገሮች እንዲያውም ሰው ሌላ ሥራ ሲያጣ የሚገባበት ሁኔታ እንዳለ ከራሳችን ሀገር ተሞክሮ ተነስተን የምንረዳው አሣዛኝ እውነታ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ አማራጭ ሲጠፋ የሚገባበት የሙያ መስክ ደግሞ ከብዙ ነገሮች አንጻር ሲታይ ስብራቱ በቀላሉ የማይጠገን ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል፡፡ የእንግሊዝ ቅኝ ተገዢ በነበረች ጉያና የምትባል የላቲን አሜሪካን ሀገር ውስጥ ታዋቂ የሥነ ጽሑፍ ባለሙያና መምህር የነበረው ብሬትዌይት የተባለ ሰው እንደተናገረው ጠቅሶ ማይክሮሶፍት ኢንካርታ የ2009 ዕትም ቀጣዩን ጥቅስ አስፍሯል፡- (የሰውዬውን ግልጽነት የማደንቅበት ሌላ አጋጣሚ ያለኝ አይመስለኝምና እዚቺው ቅንፍ ውስጥ አድናቆቴን እንድገልጥ ይፈቀድልኝ)፡፡

**I did not become a teacher out of any sense of vocation; mine was no considered decision in the interests of youthful humanity or the spread of planned education. It was a decision forced on me by the very urgent need to eat.** [ጥሬ ትርጉሙ፤ መምህር የሆንኩት በተፈጥሮ ሙያዊ ዝንባሌ አልነበረም፡፡ መምህር ለመሆን የወሰንኩት ወጣቱን ትውልድ በዕውቀት ግንባታ ለመታደግ ወይም በዕቅድ የተመራ ትምህርትን ለሁሉም ለማዳረስም አልነበረም፡፡ ምን አለፋችሁ፣ ባጭሩ መምህር የሆንኩት የርሀብ ወስፋቴን ለመሸንገል የሚያስችለኝን ዕድል ለማግኘት ነው - ለቁራሽ እንጀራ ስል!]

ጥቂት ከፍ ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው አንድ መምህር የሀገር መሠረት ነው፡፡ ካለመምህር የአንዲት ሀገር ዕድገትም ሆነ ብልጽግና ፍጹሙን ሊታሰብ አይችልም፡፡ ለሁሉም የሙያ ዘርፎች መሠረቱ ትምህርት መሆኑ አይካድም፡፡ በመምህር መሰላልነት ሽቅብ ያልተወነጨፈ የሀገር መሪ ማግኘት እንደ ተዓምር ይቆጠራል፤ በመምህር መሰላልነት ወጥቶ አብረቅራቂ የማዕረግ ጌጦችን ትከሻው ላይ ያልለጠፈ የጦር ጄኔራልና በትረ ሙሴን በዕጁ ያልጨበጠ አሮናዊ የሃይማኖት አባት አይገኝም፡፡ ሁሉም የአንድ ሀገር አንኳርና ገምቢ ዜጎች የመምህር ውጤቶች ናቸው፡፡ ስለዚህ መምህር ማለት የሀገር ዋልታና ምሰሦ ነው፡፡ በመሆኑም ለመምህርነት ሙያ ሁሉም ቢጨነቅና ቢጠበብ ሲያንሰው እንጂ አይበዛበትም፡፡ የርስዎ ልጅ ወይም የዘመድዎ ጮርቃ ሕጻን በመምህር ሥር ተኮትኩተው ነው የነገ ስብዕናቸውን የሚላበሱት፤ በመምህር ተቀርጸው ነው የነገ ሀገር ተረካቢ የሚሆኑት፡፡ ለልጆቹ የማይጨነቅ ዜጋ ደግሞ ለነገው ትውልድ ግድ የለውም ብቻ ሳይሆን ከአጥፊዎች ጋር እዬተባበረ የሚገኝ የአጥፊዎች ወገን ነው ማለት ይቻላል፡፡ በብሂላችን ‹የጨው ተራራ ሲናድ ብልኅ ያለቅስ፤ ሞኝ ይስቅ› የተባለው እዚህ ቢጠቀስ ጥሩ ገላጭ ነው፡፡ ማጋጣ መምህር በየትምህርት ተቋማቱ ተሰግስጎ ትውልድን ሲያመክን እያየን አንዳችም ነገር ላለመተንፈስ አንደበታችንን ከለጎምን እኛም የጥፋቱ ቀጥተኛ ተሣታፊዎች

መሆናችንን መርሳት አይገባንም፡፡ አዲሱ ፈሊጥ ‹አካፋን አካፋ› እንዲል ባለጌን ባለጌ በማለት በተተኪ ልጆቻችን ሕይወት የሚጫወቱ በማንኛውም የትምህርት ደረጃ መምህራን ላይ የምናስተውላቸውን ጉድፎች እንናገርና አካሄዳችንን ለማስተካከል እንሞክር -የተስፋ ጎሕ ኢትዮጵያ አባላት ‹ትውልድ ይዳን፤ በኛ ይብቃ›እንዳሚሉት፡፡

‹እንዴት እንደሚነበብ ካወቅን እያንዳንዱ ሰው መጽሐፍ ነው› የሚል ነባር አባባል አለ፡፡ ግሩም አባባል ነው፡፡ ሁላችንም መጽሐፎች ነን፡፡ መጽሐፍ ሁሉ ግን ‹በሽፋኑ አይፈረድም› - ጥሩ ወይም መጥፎ ተብሎ — ሳይነበብ፡፡

መንፈሳዊ ዐይኖቻችንን በማሣልጠን የኛንም ሆነ የሌሎችን ውስጣዊ መልካምና መጥፎ ጎኖች እንመርምርና ጠቃሚው ጎልብቶና ተሻሽሎ የሚቀጥልበትን፣ መጥፎው ተጨማሪ ጉዳት ሳያስከትል ባፋጣኝ የሚታረምበትን መንገድ መፈለግ ለመቼም የማይተው አጣዳፊ ተግባራችን ሊሆን ይገባል፡፡ በሽፍንፍን የሚተው ቁስል ለበለጠ ጉዳት እንደሚዳርግ እንገንዘብ፡፡ ይሉኝታና ግዴለሽነት ጎጂ ናቸው፡፡ ዝምታችንን የበዘበዙ ‹አጥፍቶ ጠፊ› መምህራን ክፉኛ እየጎዱን በመሆናቸው ሃይ ልንላቸው ይገባል፡፡

ወደ ተጨባጭ ምሣሌዎች ልግባና የአንዳንድ መምህራንን ገመና ልናገር፡፡ ‹ተው ቻለው ሆዴ› ብሏል ድምፀ መረዋው አያሌው መስፍን፡፡ ጉዳዩ በቀጥታም ሆነ በተዛዋሪ የሚመለከተን ወገኖች ቻል እናድርገው፡፡ ጉዳዩን ስንፈጽመው ካስቻለን ዘንድ ሌሎች ሲናገሩት ስንሰማ ደግሞ ይበልጥ ልንችል ይጠበቅብናል፡፡ ተደርጓል የተባለን ነገር ማዳመጥ ተደረገ ተብሎ የሚነገረውን ነገር ከማድረግ ያነሰ ወጪ የሚጠይቅ መሆኑን ከመረዳት በመነጨ ነው ማሳሰቢያየን ያስቀደምኩት፡፡

እንደልቡ ሸዋነሰህ ይባላል፡፡ በአንድ ዕውቅ የሀገራችን የመንግሥት ዩኒቨርስቲ ይሠራ ነበር፡፡ በ1960ዎቹ ማብቂያ ገደማ ነው፡፡ ሰውዬው በሙያዊ ዕውቀቱ አይታማም፤ሰዓቱን አክብሮ ይገባል - ይወጣልም፡፡ የማስተማር ችሎታው ማለፊያ ነው - ለተማሪ የመጠየቂያና የመወያያ ጊዜ አይሰጥም እንጂ፡፡ ቁጥብ ነው፡፡ በውል ለይተን ያላወቅነው ሥውር ኃይል የለቀቀበት የወሲብ እሳት ግን ከሰውነት ተራ አወጣውና የትም ቦታ ስናየው የሚታሰበን የጥንታዉያውኑ የግሪክና የሮም የፍቅርና የወሲብ አማልክት አፍሮዳይትና ቬነስ ሆኑ፡፡ በመሠረቱ ወሲባዊነት ጥሩ ነው፤ ተፈጥሮአዊም ነው፡፡ ገደብን አልፎ የሙያ ሥነ ምግባርን ሲጥስና የእንጀራ ገመድን ሲገዘግዝ ንጹሓንንም ላልጠበቁት አደጋ ሲዳርግ ግን ኃጢያት ብቻ ሳይሆን አመክሮ የማያሰጥ ወንጀልም ነው፡፡ ያ ሰው ወንጀለኛ ነበር፡፡ አሁን ሊያረጅ ይችላል፡፡ ተፈጥሮን ‹እምቢዬው› ብሎ ከሞገዳትም ላያረጅ ይችላል፡፡ የራሱ ጉዳይ፡፡ ነገር ግን እንዲህ ያደርግ ነበር፡-

ሰውዬው የማታም የቀንም ያስተምራል፡፡ የቀንም ትሁን የማታ ሴት ተማሪ ቀልቡ ካረፈባት አለቀላት፤ አይለቃትም! የተጣባው የቅንዝረኝነት አባዜ ነጋሪቱን ሲጎስምበት - የነዋስ አንጋችና የነአዳልሞቲ የወሲብ አዶ ከርቤ አናቱ ላይ ሲጨፍርበት የሥጋ ፍላጎቱን መቆጣጠር ይሣነዋል - ልክፍት ነው፤ ለሰማይ ለምድር የሚከብድ ትልቅዬ ሰው እኮ ነው! - ያዋጇን በጆሮ - ‹ትልቅ ፈጣሪ ብቻ ነው› እንዳትሉኝ እንጂ፡፡ ሚስት፣ ድስት፣ ቤት፣ የተሟላ ኑሮ፣ ምናምን ሁሉ የነበረው ነው - ግን ምን ዋጋ አለው ‹ዐመል ያወጣል ከመሃል› ሆነና የጉያ እሳቱን መቆጣጠር አቅቶት መሣቂያ መሣለቂያ ሆኖ ዐረፈው፡፡ የሱ ዓይነት መምህራን እጅግ ብዙ ናቸው፤ ጥፋቱ ‹መምህራን› መሆናቸው ነው—በሌላ የሙያ መስክ ቢሆን ዕዳው ገብስ ሊሆን ይችላል፡፡ ምሥኪን የሴት ተማሪዎችን በውጤት እያስፈራሩ ክብረ ንጽሕናቸውን ሳይቀር ይገፋሉ፤ ከዕጮኛቸው ይለያያሉ፤ ከትዳራቸው ያፈናቅላሉ፤ ከሩቅ ግባቸው ያሰናክላሉ፤ ለኤችአይቪ/ኤይድስና ለመሰል የአባለዘር በሽታዎች ያጋልጣሉ፤ ላልተፈለገ እርግዝና ዳርገው ዘወር በሉ ሲሏቸው አጠቃላይ የሕይወት ምህዋራቸውን እስከወዲያኛው ያዛባሉ፡፡ እነዚህን ሴትአውል ሤሰኞች ከየትምህርት ተቋማቱ መንግለን ካላወጣን በትምህርት ሥርዓታችን ላይ ከእስካሁኑ የከፋ ከፍተኛ አደጋ ማንዣበቡ አይቀርም፡፡ ያ መምህር አንድ ወቅት ለማታ ተማሪዎች አንድ ፈተና ይሰጣል፤ ልብ በሉ! መምህር ሕግ የሆነበትን፣ መምህር በፖለቲካው ዘርፍ ስማቸው በመጥፎ ከሚጠራ ከነሂትለርና ሙሶሊኒ የበለጠ አምባገነን የሆነበትን በቅርብ የማውቀውን አሣዛኝ ታሪክ ነው የምነግራችሁ፡፡

ሰውነት ቢያብጥ በምላጭ ይበጣል፤ ምላጭ ቢያብጥ በምን ይበጣል? እህል ቢያንቅ በውኃ ይዋጣል፤ ውኃ ቢያንቅ በምን ይዋጣል? ይሉ ነበር አበው፡፡ አይ ብሂል! ቆንጆ ሥነ ቃላት አሉን እኮ፡፡ ግን ማን ሊያጤናቸው? የመምህር ጥፋተኝነት ዕንቆቅልሽ የሚሆንብን እንግዲህ እዚህ ላይ ነው፡፡ ሕግን እንዲያስተምርህ የተመደበልህ ሰው ሕግን ሲያፈርስ ስታይ ምን ይሰማሃል? አያድርስ እንጂ ምንስ ቢሰማህ ምን ታደርጋለህ? ያ የታሪካችን ማዕከል ጉደኛ ‹መምህር› የፈተናውን ወረቀት አርሞ ይመልሳል፡፡ ተማሪዋ ከአንድ እኔ ከማውቀው ተማሪ አጠገብ ነበር የምትቀመጠው፡፡ ቴስቱ የታረመው ከ30 ነበር፡፡ በዚያች ተማሪ ወረቀት ላይ የተቀመጠው ውጤት ግን -3 (ኔጌቲቭ ሦስት (!) ነው) - ታይቶ የማይታወቅ አስተራረም - በታሳቢነት ተይዞ ከወደፊት ፈተና የሚቀነስ ማርክ፤ በማን አለብኝ ጀብደኝነት ላይ የተመሠረተ የዕብሪት ሥራ፡፡ የንጉሡ ነገሥት እንደልቡ ወኔና ድፍረት በዚህ ብቻ ተወስኖ አልቀረም፡፡ በዚህ ውጤት አጠገብ እንዲህ ብሎ ጽፏል፤"Come and see me in my office!" ግም ለግም እንዲሉ ሆኖ የሌሎች የተቋሙ ኃላፊዎችም ድርጊት ከዚሁ ሰውዬ ጋር ሊመሳሰል መቻሉና የ‹ዚአከ ለዚአየ› የመሸፋፈን ውለታ እንቅፋት ይሆን እንደሆነ እንጂ የርሱ የጅ ጽሑፍ መሆኑ በአባዲና ሲረጋገጥ በዚያ ወረቀት ላይ በሠፈረው ማስረጃ ብቻ ተማሪዋ መምህሩን መቅ ልትከተው በቻለች ነበር፡፡ ግና የ‹ነግ በኔ› ነገር በየትም ሥፍራ ድሩን

አድርቶ እየተጫወተብን ስለሚገኝ ፍትህን በቀላሉ ማግኘት አስቸገረን፡፡

ያቺ ተማሪ የፈተና ወረቀቷን አጠገቧ ከነበረው ሰው ጋር ስታስተያይ ምንም ልዩነት እንዳልነበረው ትረዳለች፡፡ ‹ምን ባደርግ ይሻለኛል?› በማለት ስታማክረው ‹አሃ! ምን ማድረግ ትችያለሽ? ሄደሽ የሚልሽን መስማት ነዋ! አለበለዚያ እነሱ እንደሆኑ …› ይልና ፈራ ተባ እያለ የመሰለውን ይመክራታል፡፡ በማግሥቱ ወደቢሮው ትሄዳለች፡፡ ‹ውጤትሽን አየሽው አይደል? ይህን የመሰለ ውጤት ይዘሽ የምትመረቂ ይመስልሻል? ለምንድነው የምትጠፊው? …› ይልና እንደማሽኮርመምም እንደማስጠንቀቅም ይላታል፡፡ ሞኚት ደግሞ ‹ ሁልጊዜ ነው እኮ ክፍል ውስጥ እምገኝ፤ አንድም ቀን ‹ክላስ ሚስ› አድርጌ አላውቅም፡፡ የሠራሁትን ከሌሎች ሳስተያየውም የተለዬ መጥፎ ሥራ የሠራሁ አይመስለኝም፡፡ ከእንትና ጋር ለምሣሌ አስተያይቼው አንድ ዓይነት ነው፡፡› ትላለች፡፡ ‹አይ፣ እሱ እሱን ለኔ ተይው፤ ስለአሠራሬ አንቺ አትነግሪኝም፡፡ ደግሞም የማርመው እኔ እንጂ አንቺ አይደለሽም፤ ገባሽ?› ይልና ያልገባትና የማይገባት እንዲገባት ካግባባት በኋላ በማግሥቱ አሥር ሰዓት ቢሮው ዘንድ እንድትመጣ ቀጭን ትዕዛዝ ሰጥቷት የወሲብ ጥማቱን በሚያሳብቁ ዐይኖቹ ከቢሮው ይሸኛታል፡፡ ላሳጥረው፤ የሴሚስተር ውጤት ተለጠፈ፡፡ … ከጎኗ የነበረው ልጅ ከዚያን ቀን ወዲህ ልጂቷን ጠይቋትም አነጋግሯትም አያውቅም፡፡ ሰውዬው በሌላ መንገድ እንዳይጠራጠረውና ውጤቱን እንዳያበላሽበት በመሥጋት መቀመጫውን ሳይቀር ቀይሯል፡፡

ይህ ሰው ወደቢሮ ይሄድና የሚግባባትን ጸሐፊ የአንድ ሰው ውጤት እንድትነግረው በብርቱ ተማጽኖ ይለምናታል፡፡ በሚገርም ሁኔታ - ኔጌቲቭ 3 ከ30 ያመጣቸው የዚያች ልጅ ውጤት ‹ጎጀ› ነበር፡፡ በኮሌጅ ‹ጎጆ› ማለት ‹ኤ›፣ ‹መነጽር› ማለት ‹ቢ›፣ ‹ማጭድ› ማለት ‹ሲ›፣ ‹ደጋን› ማለት ‹ዲ›፣ ‹ባንዲራ› ማለት ‹ኤፍ› ማለት ነበር በኛ የቀድሞ ዘመን፡፡ የአሁኑን አላውቅም፡፡

ተደብቆ የሚቀር ነገር የለም፡፡ እውነትን ዛሬ ብንቀብራት በራሷ መንገድ አፈሩን ገለባብጣ ነገ ትወጣለች፡፡ በተለይ መምህራን የሚያደርጓት እያንዳንዷ ነገር ለእነሱ አይመስላቸው ይሆናል እንጂ በሁሉም ተማሪ ዘንድ ቁልጭ ብሎ የሚታይ የአደባባይ ምሥጢር ነው፡፡ ሀቀኝነታቸውንም ሆነ አድሎአዊነታቸውን ተማሪዎች ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡ ምክንያቱም መምህሩ እነሱን ለማወቅ ካለው ዕድል ይልቅ ተማሪዎች እርስ በርስ ለመተዋወቅ ያላቸው ዕድል የሠፋ ስለሆነ፡፡ እነሱ እኮ ውጤቱንም ሳይቀር ተከፋፍለው ነው የሚጠብቁት፤ እስኪለጠፍ ወይ እስኪነገርም አይቆዩም - የመምህር ለማተቡ አዳሪነት በተማሪዎች ዘንድ በቅጡ የሚለካው ውጤት ሲለጠፍ ቢሆንም፡፡ የሚታወጀው ውጤት ወደተማሪዎች ግምት ከቀረበ መምህሩ ይወደዳል፤ ይመሰገናል፤ ይከበራልም፡፡ ከተማሪዎች የጋራ መግባባትና ያንንም መሠረት ካደረገ የጋራ የውጤት ግምት ከወጣ መምህሩ በሀሜት ልምጭ ይጥረገረጋል፤ በብልሹነቱ ይወቀሳል፡፡ ይህ ምግባሩም በመምህርነት ሙያው እስከቀጠለ ድረስ ለትውልደ ተማሪ ቁልቁል እየወረደ ዕድሜ ልኩን እንደጥላው ሲከተለውና ‹አይይ! እከሌ የሚባለው መምህር ደረሰህ? በል፣ እሱ እንዲህ ያለ ነገር አይወድምና ጠንቀቅ በል ወንድሜ፤ ጎመን በጤና ነው፤ ዓላማህን እንዳያጨናግፍብህ የሚወደውን ብቻ አድርግ….› እያስባለ በተማሪዎች ዘንድ እንደአባጨጓሬ ተፈርቶ ይኖራል፡፡ በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ የምናውቃቸው የመምህራን ቁጥርም የትዬ ለሌ ነው፡፡ እነሱም ዕድለቢሶች፣ በነሱ የሚማሩ ተማሪዎችም ዕድለቢሶች፤ ሀገርም ዕድለቢስ፡፡ የመምህር እንደልቡ ስንክሳር በቀላሉና በአንድ ቁጪታ ሊነበብ በሚገባው አንድ መጣጥፍ ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም፡፡ ዋናው ነገር ለእንደዚህ ዓይነቶቹ ልክስክሶች እርጅናና ሞት መኖሩ ትልቅ የተፈጥሮ ፀጋና እንደማስተዛዘኛ የሎተሪ ዕጣም ሊቆጠር የሚገባው ነው፡፡ አንዳንዴ በሕይወት ሜኑ የክንዋኔ ዝርዝሮች ውስጥ ‹እርጅናና አጃቢው ሞት ባይኖሩ ምን ይውጠን ነበር?› ብዬ ሳስበው ጭንቅ ይለኛል - እውነቴን ነው፡፡ እናም በሞት እጽናናለሁ፤ የሞት ፍ ት ሓ ዊ ነ ት በ እ ጅ ጉ ያረካኛል፤ያስደስተኝማል፡፡ከተፈጥሮ ሂደት ላናመልጥ እኛ እንደፈለግን ልንለዋውጣቸው ብንሞክርም እንኳን ሞት እንደሰው ባለመሆኑ የፊትን ይዘታ ወይም የፀጉርን ቀለም ዐይቶ አያዳላም፡፡ ተፈጥሮ ካሏት ማለፊያ ገጽታዎች ውስጥ ዋናውና የእውነተኛ ፍትህ መገለጫው ሞት ብቻ ይመስለኛል፡፡ እኔ ለምሣሌ የዛሬ 40 ዓመት ገደማ ሞት ሲይልፍ እሚነካኝም አይመስለኝም ነበር፡፡ እናም አስተሳሰቤ ግልብ አነጋገሬም እሳት እንደበዛበት ሽሮ ከላይ ከላይ የሚንተከተክ ነበረ - በስሜታዊነት የተሞላ፡፡ አሁን ግን ተመስገን ነው - ብዙ ነገር ተረድቻለሁ፤ እንደቀጣዩም ባልሆን እንደፊተኛው አይደለሁም፡፡ እናም ሞትን ሣልሞት ዐውቄዋለሁ ለማለት እደፍራለሁ፡፡ በቁማቸው የሞቱ ግን በተለያየ ምክንያት ያልተቀበሩና በዋዛ በፈዛዛ አልባሌ ተግባራት የተሠማሩ መምህራን ወገኖቼ ‹ይህችን እኔ የተረዳኋትን ያህል ስለሞት ቢረዱልኝ ምንኛ በተደሰትኩ?› የምልበት ጊዜም አለ፡፡ አምላኬ በሰማኝ! እውነቴን እኮ ነው - ሰው እንዴት ሙያውን ለወሲብና ለመሳሰለው ስብዕናን የሚያረክስ ነገር ይሸጣል? ሰው እንዴት ከመሬት ተነስቶ እወደዋለሁ ለሚለው ከፍተኛ ፣ እጠላዋለሁ ለሚለው ደግሞ ዝቅተኛ ውጤትን ይሰጣል? ሰው እንዴት አንድም መስመር የመልስ ወረቀት ሳያነብ በቀላ ጠቆረ፣ በረዘመ አጠረ፣ በከሳ ወፈረ፣ በዖታዊ ቀረቤታና በትውውቅ ግምታዊ የውጤት አሰጣጥ በሰው ሕይወት ሊፈርድ ይቃጣል? አያስጨንቅም? ሰው እንዴት የልጅ ልጁ ከምትሆን ሴት ልጅ ጋር በማርከ እየተደራደረ ካልሆነለት ‹ኤፍ እሰጥሻለሁ› እያለ አንሶላ ይጋፈፋል? ኅሊና ወዴት ገባ? የመማርስ ትርጉም ምንድነው? ሰውን ምን ነካው? እንዴ? ሲያስቡት ያሳብዳል እኮ!

በዩኒቨርስቲዎች፣ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በተወሰኑ መምህራን የሚሠራውን አጠቃላይ የውስልትና

ተግባርና ተጨባጭ ዕኩይ ድርጊቶች ስናይና ስንሰማ ‹ትምህርት እሚባል ነገር ከናካቴው ቢቀርስ?› ብለን የትምህርት አምባዎችን ልንራገም እንደርሳለን፡፡ የፍትህና የዕውቀት መፍለቂያ ሊሆኑ ሲጠበቅባቸው የጥቃቅን አምባገነኖችና የደናቁርት ማምረቻ የሚሆኑበት አጋጣሚ አይሎ ስናገኝ ተስፋ እንቆርጣለን፡፡

የመምህራን ጉድፍ ተዘርዝሮ አያልቅም፡፡ የሚያስተምሩትን ትምህርት ጠንቅቀው የማያውቁና ተዘጋጅተውም ወደክፍል የማይገቡ አሉ፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለጸው ውጤትን በዘር፣ በሃይማትና በመንደር ልጅነት አከፋፍለው ጨርሰው ከደንባዊው የውጤት አሰጣጥ አስኬል ላለመውጣት ሲሉ ለታታሪዎች የማይረባ ውጤት የሚሰጡ አሉ፡፡ ‹ባንተ ምን አገኘ?› እያሉ ጓደኞቻቸውን በመጠየቅ የሰው ልጅ የማይሻሻልና ባለበት እንደጅብራ ተገትሮ የሚቀር ይመስል አንዴ የሰጡትን ጥሩ ወይም መጥፎ ውጤት በስምና በዝና በመታወር በየሴሚስተሩ እንደታርጋ የሚለጥፉ(ፈረንጆቹ ‘Halo Effect’ የሚሉት)መምህራን አሉ፡፡ የፈተና ወረቀቶችን በጭራሽ የማያርሙ ወይም በጅምላ ዕርማት እንደነገሩ ‹እያረሙ› የሰውን ውጤት የሚያበለሻሹ/ ለሠነፍ ተማሪም ያለሥራው ትልቅ ውጤት የሚያሠክሙ አሉ፡፡ ተማሪ ሆነው እንዳላለፉ ሁሉ የሚያስተምሯቸውን ተማሪዎች የሚንቁና የሚያንኳስሱ እንደሰውም የማይቆጥሩ አሉ፡፡ በወቅታዊ መረጃ ግንዛቤያቸውን ማሳደግ የማይችሉና ያለቻቸውን የቀደመች ግን ያረጀች ዕውቀት ብቻ እየመነዘሩ ዐዋቂ መስለው ለመታየት የሚንደፋደፉ አሉ፡፡ በሣምንትና በወር ቀርቶ በዓመትም አንድም መጽሐፍ ላለማንበብ የማሉና የተገዘቱ፣ ስንቱን ዘርዝረነው … ብቻ ከሁሉም በያይነቱ አሉ፡፡ በነዚህና በሌሎችም ጠያፍ ምግባሮችና ብልሹ ባሕርያት የተተበተቡ ‹መምህራን› ባሉበት ሁኔታ የትውልድን ዕድገትና የሀገርን ሥልጣኔ ማሰብ ከእምሃበ አልቦ መና እንዲወርድ አንጋጦ እንደመጠበቅ ያህል የዋህነት ነው እላለሁ፡፡ ለመሆኑ ተማሪ ባይኖር ደሞዝ አለ? የጎልውናን ጌታ መናቅ ታዲያ ተገቢ ነው? ተማሪ ማለትስ ራሱን የቻለ ሰብኣዊ ክብር ያለው ሰው እንጂ የትልቅ ሰው ቁራጭ ወይም ስንጣሪ ነው እንዴ? የነገ ሀገር ተረካቢና ምናልባትም ከመምህሩ የተሻለ የወደፊት ተስፋ ያለው ትልቅ ሰው እንዴት የሻጉራ ይታያል? ትልቅ ነውርና ብልግናም ነው፡፡ እናስብበት፡፡

ሶደሬ ሪዞርት ሲዝናና ጦጣ ትውሰድበት የአዋሽ ወንዝ ይሞጭልፈው ሳያውቀው የጠፋበትን የተማሪ የሴሚስተር ፈተና ወረቀት ሳያርም ውጤት የለጠፈ መምህር ነበር፡፡ በዚህ ውጤትም ከትምህርት ገበታ ለጊዜው ራስዋን ያገለለች ሴት ተማሪ (የ‹withdrawal› ፎርም ሞልታ ማለት ነው) መምህሩ ከርሷ ጋር በነበረው ቆሻሻ ግንኙነት ምክንያት የ‹ኤ› ውጤት ለጠፈላት፤ አይ - የመምህር ዕዳ! ቆይቶም ከሶደሬ ወደዩኒቨርስቲው የተላከው ጠፍቶ የተገኘው የፈተና ወረቀት ያን ጉድ ገሃድ ሊያወጣው ቻለ፡፡ ይሄ ‹ወንጀለኛ›(በፍርድ ቤት ባለመረጋገጡ እንጂ ወንጀሉ ወንጀል ነው) የተቀጣው ግን ለስድስት ወራት ብቻ ከሥራ መታገድ ነበር፡፡ በሌላ መልክ ስንታዘብ - የሚገርም ነገር ነው - በአካዳሚያዊ ስኬት የላይኛውን ቆጥ ከሚቆጣጠሩት ዜጎች መካከል እንደነዚህ ዓይነቶቹ ዐይናቸውን በጨው ታጥበው የሚነሱ አጭበርባሪ ወገኖች የማይናቅ ቁጥር ያላቸው መሆናቸው ነው፡፡ ታዲያ የትምህርትን አንገት ባልተወለደ አንጀት እያረደ ያለው ማን ነው? ማንስ ነው በኃላፊነት እሚጠየቅ? ማንስ ነው የሚታደገው? ዐይነ ሥውር ዐይነ ሥውርን ሊመራ አይችልም፡፡ እንዲያ ከሆነ ተያይዞ ገደል መግባት ነው፡፡ በውነቱ ፈጥጠው እሚታዩ ብዙ ችግሮች አሉ፡፡ አንዳንዶቹ ምናልባት ዓለም አቀፋዊ ይዘት ሊኖራቸው ይችል ይሆናል፡፡ በሀገራችን የምናስተውላቸው በርካታ ችግሮች ግን ሳንውል ሳናድር መፍትሔ ልንፈልግላቸው የሚገቡን ናቸው፡፡ ይታያችሁ እስኪ - አንድ ዶክተር ሊሆን የዱክተራ ሥርዓቱ ብቻ የሚቀረው መምህር እንዲህ ማድረጉን ስትሰሙ እንደ አንድ በሽተኛ አይደለሁም ብሎ የሚያስብ ዜጋ ምን ይሰማችኋል? በሚያስተምረው ክፍል ውስጥ ተመሳሳይ ስም ያላቸው ግን አንዱ ‹ጎበዝ› ሌላው ‹ደካማ› ተብለው በመምህሩ የተፈረጁና ሌሎች ተማሪዎችም ጉዳዩን የሚያውቁት ሁለት ተማሪዎች ነበሩ፡፡ ውጤት ማስገቢያው ቀን ደርሶበት እየተጣደፈ የነበረው መምህር በግቢው ካያቸው የዚያ ክፍል ተማሪዎች አንዱን ይጠራና ‹‹ ‹ከበደ› የሚባለው ያ ጎበዙ የክፍላችሁ ተማሪ የአባቱ ስም ማን ነበር?›› ሲል ይጠይቀዋል፡፡ ተጠያቂው ግን እንደማያውቅ ይነግረዋል፡፡ በማግሥቱ ውጤት ይለጠፋል፡፡ ለ‹ጻድቃን የመጣ ለኃጥኣን ይተርፋል› እንዲሉ ያ ሠነፍና ጎሊናቢስ መምህር የሁለቱን ተማሪዎች የአባት ስም መለየት ባለመቻሉ ምክንያት ለሁለቱም ‹ከበደ›ዎች ‹ኤ› ይሰጥና የክፍሉን ተማሪ በአግራሞታዊ የሥላቅ ሣቅ ያንከተክተዋል፤ የሱ ቢጤዎችም ሺዎች ናቸው፡፡ መምህር ማለት እንግዲህ እንዲህ ነው - መምህር ከተባለ!

አንዱ ‹መምህር›ም እንዲህ አደረገላችሁ፡- ለተማሪዎቹ የቤት ሥራ ይሰጣል፡፡ ተማሪዎችም በታዘዙት መሠረት ‹ሠርተው‹ ይመጣሉ፡፡ የቤት ሥራ በባሕርይው አስቸጋሪ በመሆኑ ነው ‹ሠርተው›ን በምልክት ያላገጥሁበት፡፡ አንዱ ተማሪ ታዲያ ከወላጆቹ አንዱ መምህር ነበርና ክሽን አስደርጎ ነበር የገዛ ወላጅ አባቱን አሠርቶ የመጣው፡፡ መምህሩ የቤት ሥራዎቹን እንደነገሩ ተመለካከተና በቅድመ ፍርድ አእምሮ(Prejudice) ‹የኔ ተማሪ ይሄ ነው!› ይልና ያን ‹ጎበዝ› ተማሪ ለክፍሉ ተማሪዎች በግልጽ ያስተዋውቃል፡፡ ከአንድ መምህር እንዲህ ዓይነት ፍርደ ገምድልነት በጭራሽ አይጠበቅም፡፡ ሊማር የመጣን ሰው አስቀድመህ በነገር ጦር ወግተህ ልቡን አታደማም፤ በዚያ ዓይነት ጤንነት የሚጎድለው የማይገባ አሠራርም ቅስሙን ልትሰብር አይገባም፡፡ የሰው አመሳሶ የለውም - ሁሉም በሕግ ፊት ብቻ ሳይሆን በክፍል ውስጥም እኩል ነው፡፡ ገና ከመነሻው ፍሬን ከገለባ፣ እንክርዳድን ከስንዴ መለየት ደግሞ አይቻልም - መቼ ተማሩና!

በዚያ ላይ መምህር የመምህርነት እንጂ የነብይነት ተሰጥዖ ይኖረዋል ተብሎ አይገመትም፤ ካለውም ‹ነቢይ› እንጂ መምህር አይሆንም - ነቢይነትና መምህርነት ቦታቸው ስለሚለያይ:: ያን መምህር ያን ድፍረት የተሞላበት ትንቢት እንዲናገር ያስቻለው የምዕራብ ይሁን የምሥራቅ ፔዳጎጂ እስካሁን በውል አልታወቀም:: ብቻ ‹የሱ ተማሪ› ትምህርቱን ቀጠለ:: ሠራም አልሠራም አንዴውን ቃል ተገብቶለታልና ‹ኤ›ውን እያፈሰ ሦስቱን ሴሚስተሮች ቀጠለ:: መምህሩ በእጅጉ ስለሚፈራ ማን ተናግሮት? ‹ባንዲራ› ለማግኘትስ ማን ይደፍራል? በመጨረሻው ግን እንዲህ ሆነ:: የመጨረሻውን ኮርስ እየሰጠ ሳለ ውጤት ከመግባቱ በፊት የዚያ ክፍል የሌሎች ኮርሶች ውጤት የሠፈረበት ሮስተር እንዳጋጣሚ በዚህ መምህር እጅ ይገባል፤ በዚያም አጋጣሚ የተማሪዎችን አጠቃላይ ውጤት ያያል:: ያኔ እርሱ በመልካቸውና በቁመታቸው እየሠፈረ ያሰኘውን ውጤት ይሰጣቸው የነበሩ ተማሪዎች በሌሎች ኮርሶች ‹ኤ› ሲያገኙ ‹የርሱ ተማሪ› ግን በማጭድና በደጋን ብቻ ተጥለቅልቋል:: ያኔ መሳሳቱ ይገለጥለታል:: የመጨረሻውን ኮርስ ውጤትም እንደስከያኔው ሳይሆን በተለዬ ሁኔታ አርሞ ይገባዋል ያለውን ይሰጠዋል:: ከዚህ የምንረዳው ቁም ነገር -The moral of the story - ይህ መምህር ምንም እንኳን በማስተማር ክሂሉ የተዋጣለት ሊሆን ቢችልም ተማሪን በመገምገም ረገድ ግን ትልቅ ጉድለት የሚስተዋልበት መሆኑን መረዳት አይከብድም::

በዚህ መልክ መቀጠልና ፀሐይ ያልሞቃቸው እጅግ ብዙ የመምህራን ጉድለቶችን ከዚህም ከዚያም እየነቀሱ ማውጣት በተቻለ ነበር — ትልቅዬ ስንክሳር ይወጣዋል:: ዋናው ግን እሱ አይደለም:: ዋናው ነገር አንድ መምህር፣ መምህር ሊያሰኘው የሚችለውን የመልካም ሥነ ምግባር መገለጫዎችን ለማስመሰል ሳይሆን ከእውነት መላበስ ያለበት መሆኑን መገንዘቡና ለዚያም ስብዕና ሁላችንም መጣር የሚገባን መሆኑን መረዳቱ ላይ ነው:: ተማሪም ሙብትና ግዴታውን ዐውቆ ከፍ ሲል የተጠቀሱ የመምህራን እንከኖችን ሲያይ ለሚመለከተው የበላይ አካል የዕዝ ሰንሰለቱን (chain of command) ጠብቆ ማመልከትና ፍትሕን ለማግኘት እስከመጨረሻው መጣር ይኖርበታል::

አንዳንድ ሴቶችም ሊመከሩበት የሚገባ ደካማ ጎን እንዳላቸው መጠቆም እፈልጋለሁ:: እንደሚታወቀው ወንዶች የሚሸጡትና የሚለውጡት የውጤት ማስገኛ ‹ንብረት› የላቸውም:: ሴቶች ይህን ከተረዱ ዘንድ ወንዶች የክፍል ጓደኞቻቸውን ሊያግዙ የሚችሉበት መንገድ እንዳላቸው ይሰማኛል:: ያም ሀቀኛ መሆንና ባላቸው ‹ንብረት› ተመክተው የጎበዝ ተማሪዎችን ጥሩ ነጥብ የማግኘት ዕድል እንዳያጨናግፉ የማድረግ ‹ታሪካዊ ኃላፊነት› ነው:: ከፍ ሲል ለማስታወስ እንደሞከርኩት ሁሉም ነገር ያልፋል:: ቁንጅና ይከዳል፤ ውበት እንደጤዛ ይረግፋል፤ መልክ ይሸበሸባል፤ ፀጉር ይነጣል - ይመለጣል፤ ፊት ይገረጣል፤ ጆሮ ያዳግማል፤ ዐይን ይሠንፋል:: በሚያልፍ ውበት የማያልፍ ጸጸት መሸመት ሞራላዊም፣ ባህላዊም፣ ሃይማታዊም አይደለም:: በሥራ ያልተገኘ ውጤት ደግሞ ባዕድ ነው:: ‹የተውሶ ይመለሳል ታጥቦ ተተኩሶ› ይባላል:: የራስ ያልሆነ ነገር በሂደት ለኀሊና ወቀሣ ይዳርጋል፤ በጭራሽ አይጠቅምምም:: መምሰልና መሆን ይለያያሉ:: እናም መስለው የተገኙትን ሆነው ሊገኙ ካልቻሉ ውርደት ይከተላል:: የራስ ካልሆነ የዶክትሬት ዲግሪ የራስ ያሉት የሠርቲፊኬት ወረቀት ወይም ባዶ ንጹሕ ኅሊና በእጅጉ የተሻለ ነው:: መሳሳት ባይመከርም ሰውኛ ነው፤ አይደንቅም:: ነገር ግን ስንሳሳት ጭልጥ ባለ ሁኔታ አይሁን(ፈረንጆቹ If you have to err, err on the safe side. ብለው ሰውን እንደሚመክሩት ማለት ነው):: አንዳንዶቻችን እንሳሳታለን ብቻ ሳይሆን ሥነ ሕይወታዊ ሥሪታችን ራሱ ከራሱ ከስህተት ይመስላል፤ ባለማወቅ ብቻ ሳይሆን ሆን ብለን ስህተትን በመሥራት ሰውነታችንን የምናጎድፍ ሞልተናል:: ባይወለዱ በሚሻላቸው መጥፎ መምህራን ዙሪያ የሚከተለውን ሌላ ምሳሌ እንመልከት::

አንዲት የማውቃት የማታ ተማሪ ደብተር ሳይኖራት መነጽሯን ፀጉሯ ላይ ትሰካና የመኪናዋን ቁልፍ ብቻ እያንቃጨለች ክፍል ትመጣ ነበር:: ውጤቷ ግን በዬሴሚስተሩ በምትወስዳቸው ሦስቱም ትምህርቶች በእያንዳንዳቸው ‹ኤ› ነው:: ዐይናቸው የንጉሥ ነጋሪት እስኪያህል እያበጠ ሙሉውን ሌሊት ሲያጠኑ እሚያድሩና እሚውሉ ተማሪዎች ከማጭድና ከመነጽር ሳያልፉ እሷ ዕንቅልፏን ስትለሸልሽ እያደረች ጎጆ ጎጆውን ትልፈው ያዘች፤ ብዙዎቻችን ቀናንባት፤ አንዳንዶቻችንም እሷን መሆን አሰኘን - መሆን ላንችል:: ሦስተኛ ዓመት ስትደርስ እንደነ እንቶኔ ሣይሆን ‹ቀልድና እንትን ቤት ያበላሻል› የሚሉ ጨዋ መምህራን ገጠሟት፤ (ሙያ በልብ ብዬ እንጂ ጨዋዎች እንዳሉም ልብ ይሏል):: ያኔ ምን ታድርገው - ምንስ ይዋጣት? የቀልዱና የሰውነት ሽያጭና ግዢ ዘመን አለፈ፤ ጨረታው ተዘጋ:: በዘቀጠ ሞራል ከየልክስክሱ መምህር ባመቸ ቦታና ጊዜ ሁሉ መዳራት፣ እንደከብትም አቅልን ስቶና የይሉኝታን ገመድ በጣጥሶ ጥሎ ከጠየቃትም ሆነ በዐይኖቿ እያባበለች ወጥመዷ ውስጥ ከየምትከተው መምህር ሁሉ ጋር የመጋደም ምዕራፍም ተዘጋ:: ሦስቱንም ትምህርት ባንዲራ በባንዲራ ሆነችና በሀፍረት ተሸማቃ ከትምህርት ገበታው እስከወዲያኛው ራስዋን አሰናበተች፤ ያልጠበቀችው ዱብ ዕዳ:: ስለዚህ እንደኋለኞቹ ግሩም መምህራን ሁሉም የኅሊናው ሰው ቢሆን በመጀመሪያ ራሱ ይጠቀማል፤ ከዚያም ሀገርና የአሁኑም ሆነ መጪው ትውልድ ይጠቀማሉ:: እናም ከአድልዖና ከዘመድ አዝማድ አሠራር መቆጠብ፣ ከቅድመ ፍርድና ከጭፍን ጥላቻ ወይም የወረት ፍቅር መታቀብ (Bias, Prejudice, and Infatuation)፣ በወቅታዊ ንባብና በበቂ ዝግጅት ራስን የሙያው ባለቤት ለማድረግ ዘወትር መጣር፣

ራስን የቂም በቀልና የጥላቻ ጎተራ ከማድረግና ተማሪን በተገኘ አጋጣሚ ሁሉ ከመበቀል - በዚያም አጋጣሚ በሚገኝ ሰይጣናዊ ዕርካታ በከንቱ ከመኮፈስ መቆጠብ፣ የይቅርታና የታላቅ ስብዕና አርአያ ሆኖ ትውልድን ማነጽ ከአንድ መልካም መምህር ይጠበቃል፡፡ ምሁር ማለት መንፈሳዊ አባት እንጂ ራሱን ሰማየ ሰማያት ሰቅሎ በወገኖቹ ላይ የሚመጻደቅ ዕቡይ ዜጋ ሊሆን አይገባም፡፡ ምሁር ማለት ከማንም ከምንም ለመማር ዘወትር ዝግጁ የሆነ ትሁት እንጂ በሁሉን ዐዋቂነት ጽልመተ መንጦላዕት የሠነፎች ዐይነርግብ አእምሮውን ጋርዶ የትዕቢት ጎተራ ሊሆን አይጠበቅበትም፡፡ ዩኒቨርስቲዎች (መካነ አእምሮዎች) የዕውቀት አምባ እንጂ የደናቁርት ዋሻ ሊሆኑ አይገባም፡፡ በነዚህ ሥፍራዎች ጥናትና ምርምር እየተካሄደ ሰዎች ይበልጥ ብርሃናማ ወደሆነ ሕይወት እንዲያመሩ መንገዶች ሊመቻቹ ሲገባ ወደነዚህ መካነ ጥበብ ወኪን ቦታዎች የሚገቡ ሊቀ ሊቃውንት (ማዕምራን) በትዕቢት ጭምብል የተሸፈኑ ዕኩያን፣ በወሲብ ፈረስ የሚሠግሩ የቀትር ጂኒዎች፣ በአድልዖ የተለከፉ ፅሙማን፣ በማዕረገ ካባ ወመነሳነስ ልባቸው የሚያብጥ የመንፈስና የአእምሮ ድውያን ከሆኑ የትምህርትን ብያኔ ወይም ድፍነያ (Definition) እንደገና ልንመረምር ይገባናል ማለት ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት መጥፎ ባሕርያት በነዚያ ክቡር ወንዑድ ሥፍራዎች የሚታይ ከሆነ ደግሞ በትምህርት ብዙም ባልገፉውና እሱን ሳይደላው በርሀብ አንጀቱ በባዶ እግሩ እየሄደ በከፈለው ግብር ጥቂት ወገኖቹን ባስተማረው ማኅበረሰብ ዘንድ ሳይቀር ‹ድንቄም መማር! እንዲህም አ'ርጎ መማር የለ ጃል!› በሚል አሉታዊ ሽሙጥ እያስወቀሰ የአለመማርን ዋጋ ከመማር የሚያስበልጥ አደገኛ ሁኔታን መፍጠሩ የማይቀር ነው፡፡

በሌላ በኩል የጥሩ ውጤት ባለቤት መሆን ብቻውን የትም እንደማያደርስ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ የአንዳንድ መምህራንን የውጤት ፈደላዊ ሥርጭትና የተማሪ ውጤት ስንመለከት አስገራሚ ሁኔታዎችን እንታዘባለን፡፡ አንዳንድ ተማሪዎች ውጤታቸው ግሩም ሆኖ ተግባራቸው የትምህርት ውጤታቸውን ያዋድቀዋል፡፡ በዚያም ምክንያት ሳይሆን አይቀርም ከተቋማት ሁሉንም ውጤታቸውን ‹ኤ› አግኝተው በአራት ነጥብ ከተመረቁ በኋላ ወደሥራው ዓለም ሲሠማሩ የተማሩት ሁሉ እንደጉም እየበነነባቸው ይሁን በአግባቡ ስላልተማሩት ዕውቀትና ችሎታ እየከዳቸው ጥንታውያኑ ባለሠርቲፊኬቶቹና ባለዲፕሎማዎቹ እንደአዲስ ሲያሠለጥኗቸው አልፎ አልፎ በየመሥሪያ ቤቱ የምናስተውለው፡፡ ይህ በውነቱ በሀፍረት ሊያሸማቅቀን ይገባል፡፡ ውጤት በብላኔና በግምት ሊሰጥ አይገባም - ፍጹም ወንጀል ነው፡፡ የ‹ኤ›ንና የ‹ዲ›ን መሠረታዊ ፍቺም ያቃውሳል፡፡ እና ፍትሃዊነትን መለማመድ ቢያንስ ሰብኣዊ ክብርንና ጤናማ ኅሊናን ያጎናጽፋልና ጉዳዩ የሚመለከተው ወገን በጥሞና ቢያስብበት መልካም ነው፡፡

አንድ ዲያቆን ወደቅስና ማዕረግ ሲያድግ ማሟላት የሚጠበቅበትን መሥፈርት በሚመለከት በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ቃለ ዐዋዲ ላይ የሠፈረ

ወደ ገጽ 25 ዞሯል

## አሣባቂው ...

ከገጽ 57 የዞረ

**ፖሊሶቹ አሁንም ቁጭ ብለው ያወሩ ነበር፡፡ ጆሮዬ ውስጥ የሚጮኸው ነገር አሁን ግልፅ ብሎ ይሰማኝ ጀመር፡፡ ፍርሀቴን ለማራቅ ዘና ብዬ ለማውራት ሞከርኩ፡፡ ሆኖም ግን ጩኸቱ ጆሮዬ ውስጥ ንዳልሆነ ተ ረዳሁ፡፡**

**አሁን ይበልጥ የነጣሁ ና የገረጣሁ ሄድኩ፡፡ ከፍ ባለ ድምፅ መቀበጣጠር ቀጠልኩ፡፡ ሆኖም ያ ድምፅ የጎላ ሄደ፡፡ ና ምን ላድርግ? ድምፁ ልክ** ሆን ተብሎ **በጥጥ** ንደ ፊነ ዕንቅልፍን የሚረብሽ የሰዓት ድምጽ **ዝግ ያለ ና** አስጠሊታ **ነበር፡፡ የፖሊስ መኮንኖቹ ስካሁን ድምፁን አልሰሙትም፡፡በቂ ትንፋሽ ለማግኘት አለከለ**ክሁ፡፡ **በጣም ጮክ ብዬ ቶሎ ቶሎ ማውራቴን ገፋሁበት፡፡ ድምፁ ግን በዛው መጠን ከፍ ያለ ሄደ፡፡ ከመቀመጫዬ ተነስቼ ጮክ ባለ ድምፅ የባጥ የቆጡን መቀበጣጠር ጀመርኩ፡፡ ለምን አይሄዱም? አሁንም ሰዎቹ ድምጹን ንዳይሰሙ ከአንዱ ክፍል ጫፍ ስከ ሌላኛው ጫፍ የተንጎራደድኩ ና** ዕጆቼን **ያወናጨፍኩ ማውራቴን** ቀጠልኩ፡፡ **ኦ** አምላኬ! **ምን ማድረግ ችላለሁ? ሮጥኩ፤ ተንቆራጠጥኩ፤ የተ ቀመጥኩበትን ወንበር አንስቼ** የቀበርኩት ሬሣ ላይ ባስቀመጥኩት አነስተኛ የዕቃ ቁም ሣጥን **ላይ ጫንኩበት፡፡ ድምፁ ግን አሁንም ይበልጥ** ማስተጋባቱን **ቀጠለ፡፡ ሰዎቹ አሁንም ተረጋግተው** - በዚያ ቤት ውስጥ ምንም ያልሆነ ያህል - ተዝናንተው ወጋቸውን ይኮመኩሙ ነበር፤ ‹ምንነው እነሱን ባደረገኝ!› ብዬም ተመኘሁ፡፡ **«ድምጹን አልሰሙ ይሆን? ኦ ሁሉን ቻይ ጌ ! ሰምተዋል....ጠርጥረዋል! ሆን ብለው በፍርሀቴ ያላገጡ ነው፡፡» ብዬ አሰብኩ፡፡ ከዚህስ ስቃይ የቀረው ቢቀር ይሻላል፡፡ የሰዎቹን የማስመሰል ሳቅ ል ገሰው አልቻ ልኩም፡፡ መጮኽ ወይም መሞት ንዳለብኝ ተሰማኝ፡፡ ድምጹ የጎላ የጎላ ሄደ፡፡**

**«ከይሲ.ዎች» ብዬ ጮኩ «አ ስመስሉ! ወንጀሉን መፈጸሜን አምናለሁ፡፡** ቁም ሣጥኑን ገለል አድርጉት፤ ሣንቃዎቹንም **አንሷቸው፡፡ አዎ፣ ከዚህ ጀምራችሁ አንሷቸው፡፡ ጩኸቱ የሽማግሌው የልብ ምት** መሆን አለበት፡፡ ከአሁን በኋላ ማምለጫም የለኝም፡፡ የሆነው ሆንዋል፡፡ እንደፍጥርጥራችሁ ልታደርጉኝ እፊታችሁ ቆሜያለሁ፡፡»